# አዲስ ዘመን

እፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 103 ታኅሣሥ 13 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ

# በደላላ እየተፈተነ ያለው የእህል በረንዳ ገበያ

**በሳሙኤል ወንደሰን**

ሃምሳ ኪሎ ጤፍ ከእህል በረንዳ በሦስት ሺህ ብር ገዝቻለሁ። ይህ ዋጋ ለመንግሥት ሠራተኛ በጣም ከባድ ነው። ስለዚህ መንግሥት የገበያ ሥርዓቱን በአግባቡና በባለሙያዎች እንዲመራ እና የገበያ ሥርዓቱን ታች ወርዶ ሊመለከተው ይገባል ይላሉ የአዲስ አበባ ነዋሪው አቶ ፍሬው ካሳ፡፡

ኅብረተሰቡ ለእለት ተእለት የሚውሉ ግብዓቶችን በአቅራቢያው በተመጣጣኝ ዋጋ ሊያገኝ ይገባል የሚሉት አቶ ፍሬው፤ እየታየ ያለው የገበያ ዋጋ ግን የሚቀመስ አልሆነም፣ በተለይ የመንግሥት ሠራተኛው ደመወዝ የዋጋ ጭማሪውን መቋቋም አልቻለም ይላሉ፡፡

የዋጋ ጭማሪ ለእለት ተእለት በሚውሉ ምርቶች ላይ መደረግ የለበትም። የሀገር ውስጥ ምርቶች ላይ የሚደረገው የዋጋ ጭማሪ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን መሠረት ያደረገ አይደለም ሲሉም ነው የሚገልጹት።

የዋጋ ጭማሪ የሚደረግ ከሆነም መንግሥት ሀገራዊ ምርት ላይ ዋጋው የሚጨምርበትን ምክንያት ማወቅና ለኅብረተሰቡ ማሳወቅ ይኖርበታል። ከዚህም ባለፈ መንግሥት ለእለት ተእለት ፍጆታዎች የዋጋ ተመን አውጥቶ ሕግ የሚተላለፉ አካላት ላይ አስፈላጊውን

በደላላ እየተፈተነ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የታጣቂ ቡድኖቹ ወደ ሰላማዊ ሕይወት መመለስ የመንግሥት ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎች ፍሬ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ታጣቂ ቡድኖች በሰላማዊ መንገድ ወደሰላማዊ ሕይወት መመለሳቸው መንግሥት በተደጋጋሚ ሲያቀርብ የነበረው የሰላም ጥሪ ፍሬ ማፍራቱን ያሳያል ሲል የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አስታወቀ።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀሩን ዑመር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የክልሉ መንግስት ለቤኒሻንጉል ሕዝቦች ነፃነት ንቅናቄ (ቤህነን) ታጣቂ ቡድን በተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ ሲያቀርብ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅትም የሰላም ጥሪው ፍሬ አፍርቶ ቡድኑ በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ ተስማምቶ ወደሰላም መጥቷል፡፡

የታጣቂ ቡድኑ አባላት ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች በድጋፍ የተበረከተላቸውን የጦር መሣሪያዎች

የታጣቂ ቡድኖቹ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “ኢትዮጵያ የገጠሟትን ፈተናዎች ተቋቁማ የዓባይ ግድብን በመገንባቷ ዓለም ሊያደንቃት ይገባል”

- ላውረንስ ፍሪማን
- አሜሪካዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ተንታኝ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የገጠሟትን ታላላቅ ፈተናዎች ተቋቁማ የዓባይ ግድብን በመገንባቷ ዓለም ሊያደንቃት ይገባል ሲሉ አሜሪካዊው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ተንታኝ ላውረንስ ፍሪማን ገለጹ፡፡

ፍሪማን ከኢዜአ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ የዓባይ ግድብ ከሰሐራ በታች የተከናወነ የሚያስደንቅ

“ኢትዮጵያ የገጠሟትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ



ሲዳማ ባንክ
Sidama Bank
Bank for All!

ባንካችን የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ቅድመ-ሁኔታዎችን አጠናቅቆ በቅርቡ ሥራ ለመጀመር መዘጋጀቱን ስንገልፅ በታላቅ ደስታ ነው

አድራሻ
+25146 220 4704
+251944119303
565
+251462204704
info@sidamabanksc.com
www.sidamabanksc.com

ሲዳማ ባንክ አ.ማ.
Sidama Bank S.C.
የሁሉም ባንክ!



ካርድዎን ይሙሉ እጥፍ የጉርሻ ስጦታ ያግኙ

| ልዩ ጉርሻ | | ልዩ ጉርሻ | |
|---|---|---|---|
| 5 ብር | 10 ሜጋባይት + 10 ደቂቃ | 20 ብር | 40 ሜጋባይት + 40 ደቂቃ |
| 10 ብር | 20 ሜጋባይት + 20 ደቂቃ | 25 ብር | 50 ሜጋባይት + 50 ደቂቃ |
| 15 ብር | 30 ሜጋባይት + 30 ደቂቃ | 50 ብር | 100 ሜጋባይት + 100 ደቂቃ |
| 100 ብር | 200 ሜጋባይት + 200 ደቂቃ | | |

ሂሳብዎን ለመሙላት ወደ *705# ይደውሉ

በአብሮነት ወደፊት

Safaricom
ሳፋሪኮም




ፎቶ ፡- ከድክመንት

## “የኢትዮ-ሕንድ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በተለያዩ ዘርፎች ተጠናክሮ ይቀጥላል”

- ሮበርት ሼትኪንቶንግ
- በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር

ገጽ 4


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565




## ለአገራዊ ምክክሩ

ስኬት የማኅበራዊ መገናኛ ትስስር ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ ቀረበ

ገጽ 3

# የአቅመ ደካሞችን መንፈስ ያደሰው የቤት እድሳት

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ወይዘሮ ድንቂቱ በየነ ከአምስት ልጆቻቸው ጋር በአነስተኛዋ ቤታቸው ውስጥ በስቃይ ይኖሩ እንደነበር ያስታውሳሉ። የስቃያቸው ምንጭ ደግሞ ግድግዳዋ ከመፈራረሷ ባለፈ የፀሐይ ጨረርም ሆነ የዝናብ ጠብታን የምታሳልፈው ደሳሳ ጎጇቸው ነች።

አያድሷት ነገር የአቅሙ ጉዳይ አልሆን ቢላቸው በትካዜና በኃዘን ተውጠው ጊዜያቸውን ያሳልፉ እንደነበር ይናገራሉ። በነጋ በጠባ ክፍተቱ በሰፋው ግድግዳቸው በኩል የሚያልፈው ነፋስ ደግሞ በተኙበት አልጋቸው ላይ ሽው እያለ ለበሽታ ያጋልጣቸው እንደነበር አይዘነጉትም።

“አሁን ያ ታሪኬ ተቀይሯል፤ ቤቴም በአማረ ሁኔታ ታድሷል። ያደሱልኝ ድርጅቶች እኔና ልጆቼን በደስታ እንድንኖር ምክንያት ሆነዋል” ይላሉ።

ክረምትም ቢመጣ ፣ንፋስም ቢበረታ፤ አሁን ስጋት የለብኝም፤ ቤቴም በብሎኬት በጥሩ ሁኔታ ተገንብቷል ይላሉ። ምክንያቱም ሃቢታት ፎር ሂዩማኒቲስ ኢትዮጵያ የተሰኘው ተቋም ከኤልጂ ኤሌክትሮኒክስ ጋር በመተባበር በጉለሌና የካ ክፍለ ከተሞች ካደሷቸው የችግረኛ ቤቶች መካከል የወይዘሮ ድንቂቱ ቤት አንዱ ሆኗል።

ከዚህ በኋላ ከልጆቼ ጋር ጤናዬም ተጠብቆ በሰላም እኖራለሁ የሚሉት የ60 ዓመቷ ወይዘሮ ድንቂቱ፤ በመንደራችን የሚገኙ በርካታ ችግረኞች አሉ፤ በቀጣይም የእነሱም ቤት ተገንብቶ መንደራችን የበለጠ ያማረ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ ሲሉ ተናግረዋል።

እግሩ ላይ በደረሰ ችግር የአካል ጉዳት የተከሰተበት አቶ ተካልኝ ታደሰ ሌላኛው የቤት ዕድሳት የተደረገለት የአካባቢው ነዋሪ ነው።

“ከሁለት ልጆቼና ከባለቤቴ ጋር አብዛኛው ግድግዳና መሬቱ በካርቶን በተሸፈነ ደሳሳ ማደሪያ ውስጥ እንኖር ነበር” የሚለው አቶ ተካልኝ፤ ሌሊት ነፋስ፣ ክረምት ሲሆን ደግሞ ከነፋሱ ባለፈ ዝናብ መጣ አልመጣ እያልን የሰቀቀን ኑሮን ለዓመታት ገፍተናል። በተደረገልን ድጋፍ አማካኝነት ቤታችን ታድሷል፤ ስለዚህ ከቤተሰቤ ጋር በጥሩ ሁኔታ ለመኖር ተዘጋጅቻለሁ ሲል ደስታውን አጋርቷል።



ወይዘሮ ድንቂቱ በየነ



ወይዘሮ እልፍነሽ ሂርጳ

ከቤት እድሳቱ በተጨማሪ ለአካባቢው ነዋሪዎች ማዕድ ቤቶችን በመገንባት የአካባቢውን የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታ እና የተለያዩ የማኅበረሰብ አቀፍ ተግባራትን በማከናወን የተደረገው ድጋፍ የሚያስመሰግን ነው ያለው አቶ ተካልኝ፤ ሌሎችም ድርጅቶች ፈለጉን ተከትለው በመዲናዋ ያለውን ማኅበራዊ ችግር ለመቅረፍ ጥረት ቢያደርጉ የሚል መልዕክቱን አስተላልፏል።

“የኮሪያ ዘማች ባለቤት ነኝ፤ ባለቤቴ ካረፈ በኋላ ስድስት ቤተሰቡን የማስተዳድረው እኔ ነኝ፤ ኑሮ ደግሞ ከባድ በመሆኑ ከእጅ ወደአፍ በሆነው ኑሮ ቤቴን ማደስ እንኳን ሳልችል ዓመታትን አሳልፌያለሁ” የሚሉት ደግሞ የ65 ዓመቷ ወይዘሮ እልፍነሽ ሂርጳ ናቸው።

አሁን ላይ ድርጅቶቹ ቤቴን አድሰው አሳርፈውኛል። ቤቴ ሲጸዳ እኔም መንፈሴ ታድሷል። ለልጆቼም ምቹ የሆነ መኝታና ማብሰያ ቦታ አግኝቻለሁ። ይህ አይነት ፕሮጀክቶችም ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ በመሆናቸው ሊበራከቱ ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ቤት የታደሰላቸውን እናቶችና አካል ጉዳተኞች ደስታ ማየት በእራሱ ውስጥን ያድሳል፤ የማኅበረሰቡን ችግር ለመቅረፍ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እንደሀገር የተጀመሩ መልካም ተሞክሮዎችን የሚያጠናክሩ ናቸው የሚሉት ደግሞ የሃቢታት ፎር ሂዩማኒቲስ ኢትዮጵያ ተጠባባቂ ዳይሬክተር አቶ ዓለም ሹምዬ ናቸው።

ድርጅታቸው ከኤልጂ ኤሌክትሮኒክስ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ በተለይ በጉለሌና የካ ክፍለ ከተሞች የችግረኛ ቤቶችን ዕድሳትና የተለያዩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተለይም ከውሃና ንጽሕና አጠባበቅ ጋር የተያያዙ ፕሮጀክቶችን እያከናወነ ይገኛል ሲሉ አቶ ዓለም ያስረዳሉ።

ሰው ተኮር በሆኑ ፕሮጀክቶች የ27 ችግረኞች ቤት የማደስና ከ25 በላይ መጸዳጃ ቤትና ማዕድ ቤቶች የመገንባት ሥራ በክፍለ ከተሞቹ ይከናውናል፤ ፕሮጀክቱ ሁለተኛው ዙር ላይ የደረሰ ሲሆን ስምንት የችግረኛ ቤቶች ታድሰዋል፤ 345 ሜትር ፍሳሽ ማስወገጃና፤ስድስት ማዕድ ቤቶችና ተጨማሪ የሕዝብ መጸዳጃዎች ተገንብተው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት ውለዋል። ይህ የማኅበራዊ ኃላፊነት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ይገልጻሉ።

ከዚህ ባለፈም በትምህርት ቤቶች የእጅና ንጽሕና መጠበቂያ ፕሮጀክቶች ግንባታም እናደርጋለን። የቤትና ውሃ እንዲሁም ንጽሕና ላይ ያተኮሩት ፕሮጀክቶች ከ30 ሺህ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆናቸውን ይናገራሉ።

ከችግሩ ስፋት አንጻር ግን ብዙ ሠርተናል አይባልም። ይሁንና ጋን በጠጠር ይደገፋል ነውና የበኩላችንን ሚና ለመወጣት ጥረት ማድረጋችንን እንቀጥላለን። ሌሎችም የማኅበረሰቡን ችግሮች በሂደት ለመቅረፍ ጥረታቸውን ያጠናክሩ ይላሉ።

# ሙስናን ለመከላከል የተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር እንደሚገባ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሙስናና ሌብነትን በተለመደው አሠራር ብቻ መታገል የሚፈለገውን ውጤት ስለማያመጣ የተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር እንደሚገባ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ገለጸ፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ኤርሰኖ አቡሬ እንደገለጹት፤ በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን ለመግታት ሙሰኞች ተለይተው የሚጠየቁበትን ሥርዓትን ማጠናከር ያስፈልጋል። ሙስናና ሌብነትን በተለመደው አሰራር ብቻ መታገል የሚፈለገውን ውጤት አያመጣም፤ ለትግሉ የሕዝብ ንቅናቄ አስፈላጊ ነው ፡፡

“ኅብረተሰቡ፣ ዳኞች እና ሌሎች ፈፃሚዎች ሙሰኞችን ለመጠቆም የሚችሉባቸው መደበኛና የሞባይል ስልኮች፣ ነፃ የስልክ መስመር፣ የፌስቡክ አካውንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረገጽ እና የቴሌግራም መቀበያ ቁጥሮች ተደራሽ ለማድረግ ይሠራል” ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ሕዝብን ያሳተፈ ንቅናቄ ፈጥሮ በጋራ በመሥራት ሌብነትን ለማስቀረትና ፍርድ ቤቶችን ከሙስናና ብልሹ አሠራር ለመታደግ ተቋሙ በኃላፊነት እንደሚሠራም አረጋግጠዋል።

የክልሉ ምክር ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ ፋጤ ሰርሞሎ በበኩላቸው እንዳሉት፤ ፍርድ ቤቶች ከሙስና ነጻ ሆነው ገለልተኝነታቸው ሊረጋገጡና በሕዝብ ዘንድ አመኔታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

በሀገር ሰላም፣ ልማትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የፍትሕ ተቋማት ሚና ከፍተኛ ቢሆንም ዘርፉ የሙስና ተግባር እየተስተዋለበት መምጣቱን አመልክተው፤ችግሩ ጥቅመኞች ሕግንና ሕገመንግስታዊ ሥርዓትን ተከትለው ሕዝብን ባለማገልገላቸው የመጣ መሆኑንም ገልጸዋል።

ፍርድ ቤቶች በሕዝብ ዘንድ አመኔታ ያላቸው ተቋም እንዲሆኑ ከሙስና የፀዱና ገለልተኝነታቸው የተረጋገጠ ሊሆን እንደሚገባም አፈ-ጉባኤዋ አሳስበዋል።

እንደእሳቸው ገለጻ፤ ባልተገባ የጥቅም ግንኙነትና



አቶ ኤርሰኖ አቡሬ

ወገንተኝነት የሚሠሩ ግለሰቦችን በማጋለጥና በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማስቻል ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል።

የደቡብ ክልል ፍርድ ቤቶች ሙስናን በተግባር የመታገያና የጥቆማ ሥርዓቶች ንቅናቄ መድረክ ትናንት በወላይታ ሶዶ ከተማ ሲካሄድ በደቡብ ክልል አስር ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች የሚገኙ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችና ባለድርሻ አካላት መሳተፋቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# ድርጅቱ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ዜጎች 352 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ኮምፓሽን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ በየአካባቢው ከሚገኙ አጋር ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ጋር በመተባበር ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ዜጎች 352 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ማድረጉን አስታወቀ፡፡

የድርጅቱ የአደጋ መከላከልና ምላሽ ባለሙያ አቶ ቴዎድሮስ ገብረመስቀል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሳወቁት፤ ድርጅቱ በየአካባቢው ከሚገኙ አጋር ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ጋር በመተባበር 352 ሚሊዮን ብር በላይ ለከፋ የምግብ እጥረት ተጋላጭ ለሆኑና ከቀያቸው በሰው ሠራሽና በተፈጥሯዊ አደጋዎች ምክንያት ለተፈናቀሉ ዜጎች ድጋፍ አድርጓል፡፡

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ገለፃ፤ ድርጅቱ ድጋፉን ያደረገው በኦሮሚያ፣ በሐረሪና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች ለሚገኙ ከ81 ሺህ አራት መቶ ለሚልቁ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2022 ለከፍተኛ የምግብ እጥረት ተጋላጭ ከሆኑ አገራት መካከል እንደምትገኝ የዓለም አቀፍ የምግብ ፕሮግራምን ጨምሮ ሌሎች የሰብዓዊ ድጋፍ ተቋማት ሪፖርት እንደሚያሳዩ የገለፁት አቶ ቴዎድሮስ ድጋፉ በቀጣይም በተለያዩ መልኩ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

በትግራይ፣ በአፋር፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በተከሰቱ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ሳቢያ በርካታ ሰዎች ለምግብ እጥረት ብሎም ለአስከፊ ረሃብ እየተዳረጉና ሊዳረጉ እንደሚችሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት በማስጠንቀቅ ላይ ይገኛሉ ሲሉ አቶ ቴዎድሮስ ገልጸዋል።

በሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮችም በርካታ ወገኖቻችን ከቤታቸውና ከአካባቢያቸው ተፈናቅለው በቅርብ ወዳገኙዋቸው የመንግሥት መጠለያ ካምፖችና ጊዜያዊ መጠለያዎች ለመሰደድ የተገደዱ ሲሆን፣ በርካታ የሰብል ውድመት እንዲሁም የጋማና የቀንድ ከብቶችም



አቶ ቴዎድሮስ ገብረመስቀል

እልቂት ሊከሰት ችሏል።

“እስካሁን ባደረግነው ማጣራት በኦሮሚያ፣ በሶማሌ ፣በትግራይ፣ በአማራ፣ በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥቶች የሚገኙ ከአንድ ሺህ በሚልቁ ወረዳዎች ውስጥ አስራ ስድስት ሚሊዮን በላይ አስቸኳይ ድጋፍ የሚፈልጉ ሰዎች መኖራቸውን መረጃዎቻችን ያሳያሉ” በማለት አቶ ቴዎድሮስ አስረድተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ እ.ኤ.አ. 2020 ዓ.ም. ጀምሮ በትግራይ፣ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉልና በአፋር ክልሎች ላሉ በተመሳሳይ ችግር ለተጠቁ ከ2 ሚሊዮን ለሚበልጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች በ806 ሚሊዮን ብር በላይ የተለያዩ የሰብዓዊ ድጋፎች እና አቅርቦቶችን እስካሁን ለተጠቃሚዎች ማድረሱንም ድርጅቱ አስታውቋል።

በኢትዮጵያ አገልግሎቱን ከጀመረ 28 ዓመት የሆነው ኮምፓሽን ኢንተርናሽናል እስካሁን በሁሉም ክልሎች በሚገኙ ከ560 በላይ ፕሮጀክቶች የታቀፉ ከ135 ሺህ በላይ ሕጻናትና ወጣቶችን በማገልገል ላይ ይገኛል።

ዜና

# ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት የማኅበራዊ መገናኛ ትስስር ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ ቀረበ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የሀገራዊ ምክክሩ በኅብረተሰቡ ሰርፆ እንዲገባና ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ማምጣት ባህል እንዲሆን የማኅበራዊ መገናኛ ትስስር ባለሙያዎች የማይተካ ኃላፊነት ስላለባቸው ይህንኑ በአግባቡ እንዲወጡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጥሪ አቀረበ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከማኅበራዊ ሚዲያ ባለሙያዎች ጋር ባካሄደው ውይይት ላይ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነርና የኮሙዩኒኬሽን ክፍል ኃላፊ ዶክተር ዮናስ አዳዬ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማኅበራዊ ሚዲያ ለችግሮች መፍትሔ ለማስገኘት ትልቅ አቅም አላቸው።

እነዚህ ሚዲያዎች በሰላም ግንባታውና በምክክር ሂደቱ ላይ ጥሩ ሚናዎችን እየተወጡ ነው ያሉት ዶክተር ዮናስ፤ መልካም ዜናዎችን በማሰራጨት መሬት ላይ ያለውን እውነታ ማስረዳት ስለሚችሉ በዚህ ጉዳይ ላይ በጋራ እንሠራለን ብለዋል። ስለ ኮሚሽኑ ባልሆነ መንገድ የሚዘግቡ አካላትን የማስረዳት ሥራ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፤ አገራዊ ምክክሩ በኅብረተሰቡ ዘንድ ሰርፆ እንዲገባ፣ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ሰላማዊ እንዲሆንና ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ማምጣት ባህል እንድናደርግ የማኅበራዊ መገናኛ ባለሙያዎች ኃላፊነት አለባቸው።

ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ጦርነት ሳይሆን ሰላም ነው፤ ይህን ደግሞ የሚዲያ ባለሙያዎች ማስረዳትና አንድነትን በሚያጠናክር መልኩ መሥራት አለባቸው። ከረሃብ ለመውጣት አብረን መሥራት፣ አብሮ ለመሥራት መግባባት፤ ለመግባባት መነጋገር አለብን ብለዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ከሚዲያዎች ጋር አብሮ በመሥራትና መረጃዎችን በዘላቂነት ለኅብረተሰቡ እንዲደርሱ ከማድረግ አንጻር ኮሚሽኑ ማድረግ ያለበትን ያደርጋል፤ ኮሚሽኑ ሕዝባዊ ተቋም በመሆኑ ምክክሩ እንዲሳካ አብሮ መሥራት ጠቃሚ ነው። የሚስተዋሉ መልካም ያልሆኑ ነገሮች ካሉ መተቸትና ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተጋግዞ በመሥራት ሀገር እንድትለማ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

እንደ ሀገር የሚገጥሙ ፖለቲካዊ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና ሰላምን በቋሚነት ባህል ለማድረግ የሁሉም ዜጋ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በተለይ ማኅበራዊና መደበኛ ሚዲያዎች ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ሚዲያዎች ወጥ በሆነ መንገድ ጠንክረው በመሥራትና ከፖለቲካውና ከምክክሩ ራሳቸውን ያገለሉ እንዲመለሱ ማድረግ አለባቸው ያሉት ዶክተር ዮናስ፤ ጽንፍ የረገጡ አካላትን ወደ ምክክሩ እንዲመለሱ ማድረግ የኮሚሽኑ ዓላማ በመሆኑ ሚዲያዎች በቁርጠኝነት መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል።

ስለ ምክክር አስፈላጊነትና ምንነት በኢትዮጵያ ለምን እንዳስፈለገ ለኅብረተሰቡ ማስረዳት የሚዲያው ሥራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ኮሚሽኑ ለሚዲያዎች ቀጣይነት ያለው መረጃ መስጠት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ስለ ምክክሩ ገና ከጅምሩ ጀምሮ ባልሆነ መንገድ የሚዘግቡ የማኅበራዊ ሚዲያ አካላትን ወደ መስመር ለማስገባት ኮሚሽኑ ኃላፊነት እንዳለበት በመገንዘብ እየሠራ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ፍትሐዊ፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን መሠረት ያደረገ፣ አካታች፣ ከፖለቲካ


ዶክተር ዮናስ አዳዬ

ወገንተኝነት የጸዳ መሆኑን ሲገነዘቡ ይመለሳሉ ብለን እናምናለን ብለዋል።

ኮሚሽኑ ትክክለኛ መረጃ ለኅብረተሰቡ እንዲደርስ መረጃዎችን እያሰራጨ ነው። ከምንም በላይ ሚዲያዎች ያገባኛል፤ ሀገሬ ነው ብለው በራሳቸው ተነሳሽነት ሊሠሩ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።



# ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በግጭት ለተጎዱ 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ድጋፍ ተደርጓል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በግጭቱ ለተጎዱ ስምንት ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የተሟላ የመጀመሪያ ዙር ድጋፍ መደረጉን የብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ገለጸ።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማሪያም ከሠላም ስምምነቱ በኋላ በሰሜን የኢትዮጵያ በነበረውን የሰብዓዊ ድጋፍ አፈፃፀም እና በቀጣይ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ዙሪያ ከሰብዓዊ ድጋፍ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ተወያይተዋል። በውይይቱም የሰላም ስምምነቱ ተከትሎ በትግራይ፣ አማራና አፋር ክልሎች በግጭት ለተጎዱ ዜጎች የሚከናወነው ያልተገደበ የሰብዓዊ አቅርቦት ሒደት ተጠናክሮ መቀጠሉ ተመላክቷል።

በዚህም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በግጭት ለተጎዱ 8 ሚሊዮን 358 ሺህ 196 ዜጎች የተሟላ የመጀመሪያ ዙር ድጋፍ መደረጉን አምባሳደር ሽፈራው ተናግረዋል።

ኮሚሽነሩ አጋር አካላት ችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች የሰብዓዊ ድጋፍ ለማሠራጨት ላደረጉት ርብርብ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በቀጣይም የድጋፍ አሰጣጥ ሒደቱ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ባደረገ መልኩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

በመድረኩ በሕክምና መድኃኒቶችና በአልሚ ምግቦች አቀራረብ ላይ ተጨማሪ ጥረቶች እንዲደረጉ መጠቆሙን የኮሚሽኑ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ደበበ ዘውዴ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ በትግራይ ክልል ብቻ 29 አጋር አካላት የሰብዓዊ እርዳታ እያሰራጩ መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፥ ሌሎች በዘርፉ የተሠማሩ ተቋማትም እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል።

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረት ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት አንስቶ ታኅሣሥ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በ2ሺህ 626 ተሽከርካሪዎች አማካኝነት በሦስት የየብስ አቅጣጫዎች ለትግራይ የሰብዓዊ ድጋፍ ቀርቧል።

ከአየር ድጋፉ ባለፈ ሦስት የየብስ አቅጣጫዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ በአፋር አብአላ፣ በጎንደር-ማይጠምሪ-ሽሬ እና በኮምቦልቻ-ቆቦ-አላማጣ መስመር የሰብዓዊ ድጋፍ ኮሪደሮች መሆናቸውን ገልጿል።

እስከ ታኅሣሥ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ከ93 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ምግብ እንዲሁም ከ13 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ እንዲሁም ከ833 ሺህ ሊትር ነዳጅ ወደትግራይ ክልል መግባቱን አስታውቋል።

በተጨማሪም የፌዴራል መንግሥት 78 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ መድኃኒቶች መላኩንና የተለያዩ የሰብዓዊ ድርጅቶች በበኩላቸው 158 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት ወደ ትግራይ ማድረሳቸውን ነው የአገልግሎቱ መረጃ ያመለከተው፡፡

# በግጭት ውስጥ ለነበሩ አካባቢዎች የኮቪድ 19 ክትባት ሊሰጥ ነው

## - የኩፍኝ ክትባትም በመላ ሃገሪቱ ከዛሬ ጀምሮ ይሰጣል

**እፀገነት አክሊሉ**

አዳማ፡- ባለፉት ሁለት ዓመታት በግጭት ውስጥ ለቆዩ የትግራይ፣ አማራና አፋር ክልሎች ውስጥ ላሉ ዜጎች የኮቪድ 19 መከላከያ ክትባት ሊሰጥ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ። ከታኅሣሥ 13 እስከ 22 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስም በመላው አገሪቱ የተቀናጀ የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት በዘመቻ መልክ ይሰጣል ተብሏል።

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የብሔራዊ ክትባት ፕሮግራም አስተባባሪ ተወካይ እንዲሁም ከፍተኛ የክትባት ባለሙያው አቶ ተመስገን ለማ በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳሉት ባለፉት ሁለት ዓመታት የጸጥታ ችግር ውስጥ በቆዩ አካባቢዎች ላይ ከታኅሣሥ 13 ቀን ጀምሮ የኮቪድ 19ና የተቀናጀ የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት በዘመቻ መልክ እንዲሁም በመደበኛ የክትባት ፕሮግራም ይሰጣል።

እንደ አቶ ተመስገን ገለጻ ይህ የክትባት ዘመቻ አካባቢዎቹ በግጭት ውስጥ ከመቆየታቸው የተነሳ አሁን አንጻራዊ ሰላም በሰፈነባቸው እንዲሁም ከቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ላይ ክትባቶቹ እንደሚሰጡ አብራርተዋል።

እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በላይ የሆኑ የኮቪድ 19 በሽታ መከላከያን እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑት ደግሞ የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባትን መውሰድ እንደሚችሉ የገለጹት አቶ ተመስገን የክትባት ዘመቻው በተለያዩ ነገሮች ሊፈተን ስለሚችልም ኅብረተሰቡ ዘመቻው የተሳካ ይሆን ዘንድ ከፍ ያለ ድጋፍን ማድረግ እንዳለበትም ተናግረዋል።

ክትባቱን ለማዳረስ የመንግሥት መዋቅርን ልንጠቀም አስበናል ያሉት አቶ ተመስገን ነገር ግን መዋቅሩ ባለባቸው አካባቢዎች ላይም ቢሆን ክትባትና ተያያዥ ነገሮችን ለማድረስ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ፤በዚህ ጊዜ ውስጥ ደግሞ አጋር አካላት የምንላቸውን በመጠቀም ክትባትን ጨምሮ አስፈላጊ ግብዓቶች እንዲሄዱ እንደሚደረግም አብራርተዋል።


አቶ ተመስገን ለማ

በሌላ በኩልም ሰብዓዊ ድጋፍን እያቀረቡ ካሉ ድርጅቶች ጋር በመሆን ተደራሽ መሆን የማይቻልባቸውን ቦታዎች ለመድረስ ይሠራል ያሉት አቶ ተመስገን እነዚህ ክልሎች የግድ መከተብ ወይም አገልግሎቱን ማግኘት ስላለባቸው በየትኛውም መንገድ ቢሆን እነሱ ጋር የመድረሱ ሥራ ይሠራልም ብለዋል።

ይህንን ዘመቻ የማስተባበሩ ሥራ በሚኒስትሮችና በከፍተኛ አመራሮች የሚመራ ነው ያሉት አቶ ተመስገን፤ በመሆኑም በችግር ውስጥ የቆዩ ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሁሉ አገልግሎቱን ያገኛሉ የሚል እምነት መኖሩን አውስተዋል።

በሌላ በኩልም የተቀናጀ የኩፍኝ መከላከያ ክትባት ዘመቻ ላይ ከተወለዱ ጀምሮ ምንም ዓይነት ክትባት ያልወሰዱ ፣ ጀምረው ያቋረጡ ሕጻናት ልየታና ክትባት የሚሰጥ ሲሆን ጎን ለጎንም የአጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታ ፣የቫይታሚን ኤ ጠብታ እደላ ፣የአንጀት ጥገኛ ትላትል መድኃኒት እደላ ፣ ከወሊድ ጋር የታያያዘ የፌስቱላ ችግር ልየታና የኮቪድ 19 ክትባት እንደሚሰጥ ተናግረዋል።

ኅብረተሰቡም ይህንን አውቆ ከዚህ ቀደም የተከተቡም ያልተከተቡትንም ሕጻናት በማስከተብ አጋርነቱን እንዲያሳይ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ዜና



# “የኢትዮ-ሕንድ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በተለያዩ ዘርፎች ተጠናክሮ ይቀጥላል”

ሮበርት ሼትኪንቶንግ

በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር

**በዘካርያስ ወልደማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ እና የሕንድ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በትምህርት፣ በኢንቨስትመንት እና በመከላከያ ዘርፎች ተጠናክሮ እንደሚቀጥል በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር አስታወቁ፡፡

የኢትዮጵያ እና የሕንድ 75ኛ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የምሥረታ በዓልን ምክንያት በማድረግ በኢትዮጵያ የሕንድ ኤምባሲ ባዘጋጀው የሚዲያ ዝግጅት ላይ በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር ሮበርት ሼትኪንቶንግ እንደተናገሩት ኤምባሲው የሁለቱን ሃገራት የቆየ ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግ እየሠራ ነው፡፡

ከነዚህም ውስጥ አንዱ የሁለቱን ሃገራት ባህላዊ ግንኙነት ለማጠናከር በተለያዩ ክልሎች እና ቦታዎች በርካታ የባህል ፕሮግራሞችን እያካሄደ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በትምህርት ዘርፍ ሕንድ እና ኢትዮጵያ ጥሩ ግንኙነት የመሠረቱ መሆኑን የጠቀሱት አምባሳደር ሮበርት፣በአሁኑ ወቅት በሕንድ ውስጥ ከሚማሩት አፍሪካውያን ተማሪዎች መካከል በርካታውን ቁጥር የያዙት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት ከኤምባሲው ባልደረቦች ጋር በመሆን ከ25 ያላነሱ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎችን መጎብኘታቸውን የተናገሩት አምባሳደሩ የሕንድ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ኤምባሲው ባለፈው ዓመት ከሰጣቸው 55 የትምህርት እድሎች ውስጥ 48ቱ በዘርፉ ያለውን የመምህራን እጥረት ለመቅረፍ የሚያስችል የፒኤችዲ ፕሮግራሞች እንዲሆኑ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

በኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተመዘገቡ 650 የሕንድ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ መኖራቸውን የጠቀሱት አምባሳደሩ፤ ከነዚህም 300 ያህሉ በተግባር በሥራ ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

“እኔ ራሴ ከ160 በላይ የሕንድ ፋብሪካዎችን ጎብኝቻለሁ፣ አብዛኞቹ በአዲስ አበባ እና አካባቢው የሚሠሩ ሲሆን፣ 100 ያህሉ በኦሮሚያ ውስጥ ናቸው። በደብረ ብርሃንም ከ 12 እስከ 15 የሚደርሱ ፋብሪካዎች አሉን። ትልቅ የሙዝ እርሻ እንዲሁም ትልቅ የስኳር ፋብሪካ በሕንድ ኩባንያዎች እየተከናወነ ነው” ሲሉም አምባሳደር ሮበርት ጠቁመዋል፡፡

እንደ ኮሚሽኑ መረጃ የሕንድ ኢንቨስትመንቶች ድምር አኀዝ 5 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሦስት ቢሊዮን ያህሉ ሥራ ላይ ውሏል። ለ75,000 ኢትዮጵያውያንም የሥራ እድል ፈጥረዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ መንግሥት ኢንቨስትመንት በተመለከተ በጣም አወንታዊ ሕጎችን አውጥቷል፣ ይህም የሕንድ ኢንቨስትመንቶች እዚህ እንዲኖሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

በ1960ዎቹ ሕንድን የጎበኙት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በሕንድ ወታደራዊ አካዳሚ ተደንቀው ተመሳሳይ ወታደራዊ አካዳሚ በኢትዮጵያ እንዲቋቋም ጠይቀው እንደነበር አምባሳደር ሼትኪንቶንግ አስታውሰዋል። የሐረር ወታደራዊ አካዳሚም የሕንድ ወታደራዊ አካዳሚ አምሳያ ሆኖ የተቋቋመ ሲሆን የመጀመሪያዎቹ ሦስት አዛዦች ከሕንድ የመጡ እንደነበሩም አምባሳደሩ ጨምረው ተናግረዋል።

“የመጨረሻዎቹ የሕንድ ወታደራዊ አስተማሪዎች በኢትዮጵያ ሲሠሩ እንደነበር አምባሳደሩ አስታውሰው፤ በመከላከያ ዘርፍ የምናደርገው ትብብር ቀጣይ እንደሚሆንም አምባሳደሩ አረጋግጠዋል፡፡

ሕንድ ካለፈው ታኅሣሥ ወር ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል የቡድን 20 አባል ሀገራት ፕሬዚዳንትነትን የተረከበች መሆኑን አምባሳደሩ አስታውሰዋል፡፡

# በደላሳ እየተፈተነ ያለው የእህል...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል ሲሉም ያሳስባሉ።

እንደዚህ አይነት ችግሮች የሚፈጠሩት የገበያ ሥርዓቱ በአግባቡና በባለሙያዎች እየተመራ ባለመሆኑ ነው ያሉት ደግሞ ካሳሁን በላቸው (ስማቸው የተቀየረ) የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው።

አብዛኛውን ጊዜ ኅብረተሰቡ ለዋጋ ጭማሪና ለኑሮ ውድነት የሚጋለጠው በንግድ ቦታዎች የሚገኙ ሕገወጥ ነጋዴዎች በሚፈጥሩት አሉታዊ እንቅስቃሴ ነው። ይህም ደግሞ ነጋዴዎች የፈለጉት ምርት ላይ የሚፈልጉትን ዋጋ እንዲጨምሩ እድል ፈጥሮላቸዋል ይላሉ።

መንግሥት የኢኮኖሚ ችግሮችን ካልፈታ እንደሀገር ትልቅ ጉዳት ያስከትላል። ችግሩን ለመቅረፍ ደግሞ ኅብረተሰቡ፣ መንግሥትና የሚዲያ አካላት በአንድ ላይ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ባይ ናቸው።

የአዲስ አበባ የእህል ነጋዴዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሐጂ ሳኒ ሁሴን እንደሚናገሩት፤ በአዲስ አበባ እህል በረንዳ ገበያ ሕገወጥ ነጋዴዎች ይበዛሉ፡፡ ነጋዴዎቹ እህል ከየት እንደሚያስገቡ፣ እንዴት እንደሚሸጡና ምን ያህል ትርፍ እንደሚያገኙ አይታወቅም፣ የንግድ ፍቃድም የላቸውም።

በሕገወጥ ንግድ ምክንያት መንግሥት ከዘርፉ የሚገባውን ግብር እየሰበሰበ አለመሆኑን፤ ሸማቹ በሚገዛቸው እህሎች ላይ የዋጋ ጭማሪ እየተደረገበት እንደሆነ እና ሕጋዊ ነጋዴው የሚገባውን ጥቅምና መብት እያገኘ አለመሆኑንም ነው የሚገልጹት ፡፡

ማህበሩ የነጋዴውን፣ የሸማቹንና የመንግሥትን ጥቅም ለማስከበር እና ሕገወጥ ንግድ እንደሀገር የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ እየሠራ ነው ያሉት ሐጂ ሳኒ፤ መንግሥት ከማኅበሩ ጋር በጋራ ቢሠራ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብና የዋጋ ንረቱን መቆጣጠር እንደሚቻል ይጠቁማሉ፡፡

እንደ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ገለፃ፤ በንግድ ሥርዓቱ ላይ ምንም እሴት የማይጨምሩ ደላሎች ችግሩን እያባባሱ ነው። የወፍጮ ቤት ባለቤቶችና የችርቻሮ ነጋዴዎች ያለደረሰኝ ገዝተው ከፍተኛ ጭማሪ እያደረጉ ያለደረሰኝ በመሸጥ በግብርና ምርቶች ላይ ተጽዕኖ እያሳረፉ ነው።

የንግድ ሥርዓቱ ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ በሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ እንዲፈጠርና እንዲባባስ እንዲሁም የኑሮ ውድነት እንዲፈጠር እያደረገ በመሆኑ መንግሥት በሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ መውሰድ አለበት ብለዋል።

የሕገወጥ ንግድ ላይ ያሉትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ያለው ቅንጅታዊ ሥራ ክፍተት አለበት። ሕጋዊ ነጋዴውም ከሕገወጥ ነጋዴዎች ጋር ተወዳድሮ መሥራት አልቻለም። ለዚህም መንግሥት በሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ የሚያደርገውን የቁጥጥር ሥርዓትን በማጠናከር እና በማዘመን መከላከል አለበት ሲሉም አሳስበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የሕግ ማስከበር ዘርፍ ኃላፊ ኮማንደር አሕመድ መሐመድ በበኩላቸው፤ አብዛኛዎቹ የእህል በረንዳ ነጋዴዎች ከአዲስ አበባ ውጭ የሚመጡ ናቸው። ይህም ማለት የአዲስ አበባ ነጋዴ ያልሆኑ ከክልል የሚመጡ ነጋዴዎች አሉ ማለት ነው። ከዚህም ባለፈ በአካባቢው በንግድ ሥርዓቱ ላይ ምንም እሴት የማይጨምሩ ደላሎችም ይገኛሉ ይላሉ።

እንደሀገር በአካባቢው ያለው የንግድ ሥርዓት ግልጽነት የጎደለው ነው። እንደገቢዎች ቢሮ ደረሰኝና ቁጥጥር ማድረግ የምንችለው ሕጋዊና የንግድ ፍቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ላይ ነው። ለእርምጃና ለቁጥጥር እንዲመች እህል በረንዳው በብሎክ ተከፍሏል። ይህም አካባቢው ላይ የሚሠሩ ሥራዎችን በቅርበት ለመሥራት ያስችላል።

አሁን ላይ የገቢዎች ቢሮ እየተቆጣጠረ ያለው ንግድ ፍቃድ አውጥተው የሚሠሩትን ነው ያሉት የሕግ ማስከበር ዘርፍ ኃላፊው፤ ለዚህም በሕጋዊ መንገድ የማይሠሩ፣ ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ደላሎችና ነጋዴዎች ወደ ሕጋዊ መንገድ የሚገቡበትና ለቁጥጥር የሚያመች ሥርዓት ለመዘርጋት ከንግድ ቢሮ ጋር በጋር እየሠራን ነው ብለዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ቅድስት ስጦታው እንዳሉት፤ በአዲስ አበባ እህል በረንዳ አካባቢ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድና መሸጫ ቦታ ያላቸውን እየተቆጣጠርን ነው። ነገር ግን የአዲስ አበባ ንግድ ፍቃድ የሌላቸው ነጋዴዎች አሉ።

እነዚህ አካላት ሕጋዊ ነጋዴው ላይ ጫና እየፈጠሩ እንደሆነ አውቀናል። ይህንንም ለመፍታት ከተለያዩ አካላት ጋር በጋራ እየሠራን ነው። ሆኖም እርምጃ መውሰድ አዳጋች ነው። ምክንያቱም ኢኮኖሚው ላይ የሚፈጥረው የራሱ ተጽዕኖ አለው ብለዋል፡፡

በቁጥጥሩ ነጋዴዎቹ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ያላቸው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ስለሆነ ወደ ሕጋዊ መስመር የሚመጡበት ሥርዓት እየዘረጋን ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ መንግሥትም ከግብር ጋር ተያይዞ እስከ አሁን ያጣውን ገቢ እንዲያገኝ እየሠራን ነው ብለዋል። ኅብረተሰቡም የቢሮውን ጥሪት በመደገፍ ያለደረሰኝ ከመግዛት እንዲቆጠብ አሳስበዋል።

# የታጣቂ ቡድኖቹ ወደ ሰላማዊ ሕይወት መመለስ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በመፍታት ላይ ናቸው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ለታጣቂዎቹም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተሐድሶ ስልጠና መስጠት መጀመሩን አስታውቀዋል።

የተሐድሶ ስልጠናው ወደ ሰላማዊ የልማት እንቅስቃሴ ለመግባት የሚረዳ ነው ያሉት የፖሊስ ኮሚሽነሩ፤ ታጣቂዎቹ ስልጠናውን ወስደው ሲያጠናቅቁ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንዲሰማሩ የክልሉ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ከታጣቂ ቡድን ጋር የተደረሰው የሰላም ስምምነት በቀጠናውና በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍ እንዲሁም ለሕዝቦች የላቀ ተጠቃሚነት ድርሻው የላቀ መሆኑንም አመላክተዋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ኢስሃቅ አብዱልቃድር በበኩላቸው፤ የክልሉ መንግሥት በተደጋጋሚ ለቡድኑ ሲያቀርብ የነበረው የሰላም ጥሪ በመጨረሻ ውጤት አግኝቷል ብለዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት በክልሉና ድንበር አካባቢ ሲንቀሳቀስ ከነበረው ታጣቂ ቡድን ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ያካሄደው የሰላም ስምምነት ለክልሉና ለሀገር ሰላም የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑንም አቶ ኢስሃቅ ጠቁመዋል።

ታጣቂዎቹን ወደሰላማዊ እንቅስቃሴ ለማስገባት የተደረገው ጥረት በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ በቀጣይ የሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ርምጃ ነው ብለዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ልዩነቶችን በመነጋገርና በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በትኩረት እየሠራ መሆኑንም አቶ ኢስሃቅ ገልፀዋል።

የቤኒሻንጉል ሕዝቦች ነፃነት ንቅናቄ (ቤህነን) መሪ አብዱልወሃብ መህዲ ኢሳ በበኩላቸው፣ ከመንግሥት ጋር በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሠረት በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ሕዝቦች በሁሉም ዘርፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩላችንን ድርሻ እንወጣለን ብለዋል።

በቀጣይም እርስ በእርስ መወነጃጀልን በማቆም ለጋራ ልማትና ዕድገት መሥራት ከሁሉም ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

ሕዝቡ ለሰላም የሚሰጠው ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ታጣቂዎቹ ወደሰላም ሲመለሱ በየአካባቢው በተደረገላቸው ደማቅ አቀባበል ደስተኛ መሆናቸውንም አብዱልወሃብ መህዲ ኢሳ ገልፀዋል።



**የቤኒሻንጉል ክልል መንግሥትና የቤኒሻንጉል ሕዝቦች ነፃነት ንቅናቄ (ቤህነን) ታጣቂ ቡድን የሰላም ስምምነት**



**ለቤኒሻንጉል ሕዝቦች ነፃነት ንቅናቄ (ቤህነን) ታጣቂ ቡድን የተሐድሶ ሰልጠና ሲሰጥ**

# “ኢትዮጵያ የገጠሟትን ፈተናዎች ተቋቁማ የዓባይ ግድብን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ስኬት የታየበት ፕሮጀክት ነው፤ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበትን ዘርፈ ብዙ ፈተና ተቋቁሞ የአፍሪካን አህጉር ሊጠቅም የሚችል ታላቅ ግድብ መገንባት በመቻሉ አድናቆት ሊቸረው ይገባል፡፡

በያዝነው ሳምንት መባቻ የዓባይ ግድብን የጎበኙት ተንታኙ፤ የትኛውም አካል ግድቡ መገንባቱን አስመልክቶ ማማረር የሚችልበት ምክንያት የለውም ብለዋል፤ ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የተደቀኑባቸውን ተግዳሮቶች ተቋቁመው በአፍሪካ ታላቅ የሆነውን እና በዓለም አቀፍ ደረጃው ሰባተኛ የሆነውን ከሰሐራ በታች ታላቅ ክስተት በማከናወናቸው ዓለም እንኳን ደስ ያላችሁ ሊላቸውና ሊያደንቃቸው ይገባል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

“በፈጣን የግንባታ ሂደት ላይ ባለው የዓባይ ግድብ እንደተገኘ አንድ አሜሪካዊ ደስተኛ አለመሆን አልችልም” ሲሉም አክለዋል፡፡

ግድቡ ሲጠናቀቅ ከሰሐራ በታች ካሉ ሀገራት ኢትዮጵያ ደቡብ አፍሪካን ተከትላ ሁለተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል አመንጭ ትሆናለች ያሉት ፍሪማን፤ በዚህም ኢትዮጵያ በአሜሪካ እና በምዕራባውያን ሀገራት እንኳን ደስ ያለሽ ልትባልና ልትደነቅ ይገባል ሲሉ በአጽንዖት ገልጸዋል፡፡

“እኔ እንደማስበው አሜሪካ እና የምዕራባውያን መንግሥታት ኢትዮጵያን ማሞገስ አለባቸው” ያሉት የፖለቲካና ኢኮኖሚ ተንታኙ፤ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግም መንገዶችን ሊፈልጉ ይገባል ብለዋል፡፡

ፍሪማን እንደገለጹት፤ አፍሪካ ከዚህ የበለጠ የትየለሌ የኢነርጂ መሠረተ ልማት ያስፈልጋታል፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ እየገነባችው ያለው የዓባይ ግድብ እንደ አንድ የመጀመሪያ እርምጃ የሚታይ ነው፡፡ ኢትዮጵያም ለዚህ የሚያስደንቅ እና የሚያምር ስኬቷ በዩናይትድ ስቴትስ እና በምዕራቡ ዓለም መደነቅ አለባት፡፡

“ዛሬ እዚህ መገኘቴ በእኔ የጉልምስና ዘመን ጊዜ ውስጥ ልዩ ጊዜ ነው፡፡ እኔ እንደማስበው ዩናይትድ ስቴትስ እና የምዕራባውያን መንግሥታት ኢትዮጵያ የያዘችውን የግድብ ሥራ እያወደሱ፤ ኢኮኖሚዋን የምታሳድግበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው።” ያሉት ፍሪማን ምዕራባውያን፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የዓባይ ግድብን የሚገነባው የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ ካለው ፍላጎት መሆኑን መረዳት ይገባቸዋል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

አሜሪካዊው ተንታኝ እንዳሉት፤ አሁን ያለው ትውልድ በዓባይ ግድብ ላይ ያስመዘገበው ድል ከቅድመ አያቶቹ ድል ጋር የሚነፃፀር ነው፡፡

“በዳግማዊ ምኒልክ የተመሩት ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ጦርነት የጣሊያንን ጦር አሸንፈዋል፡፡ አንድ የአፍሪካ ሀገር ዘመናዊ የሚባልን ጦር ድል ሲያደርግ የመጀመሪያው ነበር፡፡ ይህም ኢትዮጵያ በጭራሽ ቅኝ ተገዢ እንዳትሆን አድርጓታል። ይህ የኢትዮጵያውያን ሥነ ልቦና ለወደፊቷ ኢትዮጵያ ራዕይ ጠንካራ መሠረት ነው፡፡ የዓባይ ግድብም ተመሳሳይ የሥነ ልቦና ጥንካሬ ውጤት ወካይ ማሳያ ነው፡፡” ሲሉ አብራርተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለጤናማ ትውልድ ግንባታ ሁሉም ኃላፊነቱን ይወጣ!

ከመድኃኒት አጠቃቀም ቁጥጥር ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ሊያስከትሉ የሚችሉት ችግር ዘርፈ ብዙ እንደሚሆን ይታመናል።ለዚህም ሲባል አገራት በመድኃኒት አጠቃቀም ዙሪያ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ይንቀሳቀሳሉ።

ከአመራረት የሚጀምረው የቁጥጥር ስርዓቱ መድኃቶች ገበያ ላይ ውለው ተጠቃሚዎች ጋር የሚደርሱበትን መንገድ በጠንካራ ዲሲፕሊን የሚከታተል ነው፤ ክፍተቶች ሲያጋጥሙም የሚወሰዱ ርምጃዎችም ችግሩ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ታሳቢ ያደረጉና የማያዳግም ሊሆኑ እንደሚገባ ይታመናል ።

በተለይም ባለንበት ዘመን የመድኃኒት ጥቁር ገበያን ጨምሮ መድኃኒቶችን ላልተገቡ ተግባራት /ያለ ባለሙያ ትዕዛዝ የመጠቀሙ ልምምድ እያደገ መምጣቱ ፤ ችግሩ በአገራት ኢኮኖሚ ላይ ብቻ ሳይሆን የጤናማ ትውልዶች ግንባታ ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ይገኛል ።

ችግሩ በእኛም አገር አድማሱን ዕለት ተዕለት እያሰፋ አገራዊ ስጋት ከመሆን አልፎ ጤናማ ትውልድ ለመገንባት በሚደረገው ብሄራዊ ጥረት ላይ የሚታይ አደጋ በመሆን ላይ ይገኛል። በዜጎች ላይ በተለይም የነገ አገር ተረካቢ ትውልዶች ላይ እያስከተለ ያለውም ጥፋት በቀላሉ የሚሰላ አይደለም ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፋርማሲዎች አካባቢ በስፋት እየተስተዋለ የሚገኘው መድኃኒቶችን ያለባለሙያ ትዕዛዝ / ከሙያው ስነ ምግባር ውጪ የመሸጥ ሁኔታ መድኃኒቶች ከሚፈጥሩት የጎንዮሽ ችግር ባለፈ ፤ ከተፈበረኩበት አገልግሎት ውጪ እንዲውሉ በማድረግ አገራዊ የጤናማ ትውልድ ግንባታው ተግዳሮት በመሆን ላይ ነው።

ቀደም ባለው ጊዜ ትራማዶል የተባለው መድኃኒት ያለ ሃኪም ፈቃድ ገበያ ላይ በስፋት በመገኘቱ የነገ አገር ተረካቢ ትውልድ ላይ የቱን ያህል የጤና አደጋ ስጋት ምንጭ እንደሆነ በመዘገብ ለችግሩ ትኩረት እንዲሰጠው ማሳሰባችን ይታወሳል።

በትናንትናው ዕትማችን ደግሞ ድንገተኛ ጽንስ እንዳይፈጠር የሚከላከለው ፖስት- ፒል እና ቪያግራ የተሰኘው የስንፈተ ወሲብ መድኃኒት በየፋርማሲው ያለ ሃኪም ፈቃድ በቀላሉ መገኘታቸው በአገር ተረካቢው ትውልድ ላይ አሁነኛ የማህበራዊና የጤና ስጋት ምንጮች መሆናቸውን የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር ዘግበናል።

እንደ ጤና ባለሙያዎች ገለጻ ከሆነ ፤ ፖስት- ፒል የተባለው መድኃኒት ታዳጊ ሴቶች ያለእድሜያቸው የወሲብ ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ፤ በትምህርታቸው ፤ በማህበራዊ ሕይወታቸው ከዚያም ባለፈ አጠቃላይ በሆነው ህይወታቸው ላይ ተግዳሮት ሊሆን የሚችል አቅም እንዳለው ተናግረዋል፤ በቀጣይ ጤንነታቸው ላይም ሊያስከትል የሚችለው የጎንዮሽ ችግር በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ቪያግራ የተሰኘውን የስንፈተ ወሲብ መድኃኒት በተመሳሳይ መንገድ በገበያ ላይ ያለ ባለሙያ ፈቃድ በስፋት መገኘቱ ታዳጊ ወንዶች ባልተገባ መንገድ መድኃኒቱን እንዲጠቀሙ እያደረጋቸው ይገኛል፤ ይህም በራሱ ሊያስከትል የሚችለው የጎንዮሽ ችግር ውስብስብና ከፍ ያለ ነው።

ይህ ዘገባ የመድኃኒት ገበያ ቁጥጥር ክፍተቱ በአደባባይ የመነጋገሪያ ርዕስ ጉዳይ ባደረጋቸው መድኃኒቶች ላይ ብቻ የሚታይ ሲሆን፤በተለያየ መንገድ ወደ አገርውስጥ ገብተው በደላሎች በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጡ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ መድኃኒቶችን የሚያካትት አይደለም።

የፋርማሲ ባለሙያዎች በስፋት እየተሳተፉበት ያለውን ይህን እንደ አገር ጤናማ ትውልዶችን ለማፍራት እየተደረገ ያለውን ጥረት አደጋ ውስጥ እየከተተ ያለን ችግር ፤ በጠንካራ የቁጥጥር ስርዓትና የማያዳግም እርምጃ ማስቆም ካልተቻለ በቀጣይ ሊያስከትል የሚችለው ጥፋት የከፋ እንደሚሆን ይታመናል።

ችግሩን ለማስቆም በአገር አቀፍ ደረጃ በመድኃኒቶች ላይ ተገቢውን ሙያዊ ቁጥጥር ለማድረግ የተቋቋሙት የፌደራልም ሆነ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የመድኃኒት ቁጥጥር ተቋማት የተሰጣቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል። በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን አሸንፎ መውጣት የሚያስችል ቁመና መላበስም ይጠበቅባቸዋል።

ተቋማቱ ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር ችግሮች በዚህ ደረጃ ገዝፈው አደባባይ እስኪሞሉ ድረስ መፍትሄ መሆን ያለመቻላቸው እውነታ፤ አገራዊ ሆነ ተቋማዊ የቁጥጥር ስርዓቶቹን በአግባቡ እንዲፈተሹ የሚያስገድድ ነው። ከዚህም ባለፈ ተቋማቱ ወቅታዊ ችግሮችን ፈጥኖ መለየትና ለችግሮቹ መፍትሄ መፈለግ የሚያስችል አቅም መገንባት እንደሚኖርባቸውም የሚያመላከት ነው።

ወላጆች፣ ትምህርትቤቶች፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጸጥታ አካላትም ትውልድን ለመታደግ ካለባቸው ከፍተኛ ኃላፊነት አንጻር ተመሳሳይ ችግሮችን በእንጭጩ ለመቅጣት ብዙ ሥራ እንደሚጠብቃቸው መረዳት ይኖርባቸዋል። ለዚህ የሚሆን ዝግጁነትና ንቁ ተሳትፎም ይጠበቅባቸዋል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ሙስናን ለመዋጋት የተጀመረው ዘመቻ ስኬታማ እንዲሆን

**ከትዝታ ማስታወሻ**

ፒያሳ፣ ሸዋበር፣ መናኸሪያ እና ሌሎችም ሥሞች በአገራችን የቆዩና በአቅራቢያው የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ተንተርሰው የሚሰጡ መጠሪያዎች ናቸው።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን የሙስና (የሌብነት) እና የሙሰኞች (የሌቦች) ቁጥር መጨመርን ተከትሎ በአብዛኛው የአገራችን ከተሞች የመጣ የሰፈር ስያሜ ‹‹ሙስና ሰፈር›› ይሰኛል፡፡

ይህ ሰፈር ታዲያ በአንጻራዊነት ከተማው ውስጥ ከሚገኙት ሰፈሮች የተዋበ ነው፤ የውበቱም ምንጭ ከሙስና የተገኘ ሃብት መሆኑ ይታመናል።በዚህ ሰፈር የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች ከውበታቸው በተጨማሪ የተሟላ መንገድ በአንጻራዊነት የማይጠፋ መብራት ተጠቃሚዎች ናቸው።‹‹ለሃጥዕ የመጣ ለጻድቃን ይተርፋል›› እንደሚባለው ሳይሆን ለተመረጡት የመጣ በረከት ለሌላውም ተርፎ ለእነሱ ሲባል የአካባቢው ፀጥታም አስተማማኝ ነው።

ጉቦ መስጠትም ሆነ መቀበል፤ ሥራን በዘመድ፤ በብሔር ወይም በሃይማኖት ጥላ ሥር መፈለግ የተለመደ የዘወትር ትዕይንት ሆኗል።የአገር ሃብት የዘረፉ ሌቦችን፤ ሙሰኛ፣ ኪራይ ሰብሳቢ፣ እያልን በማንቆለጳጰስ ዓመታትን አስቆጥረናል። ይህም ድርጊቱ እንዲስፋፋ ከማስቻሉ ባለፈ የተፈቀደ ያህል እንዲሆን አስችሎታል።

አሁን አሁን (ከለውጡ ማግስት ጀምሮ) ችግሩን ሕብረተሰቡ ባልለመደው ቃል ተሳስቶ ሲያሳንሰው ከመመልከት ወጥተን ድርጊት ፈጻሚዎቹን ሌቦች ድርጊቱንም ሌብነት ብሎ መጥራት ጀምረናል። ይህም በራሱ ችግሩን ለመዋጋት አንድ እርምጃ እንደሆነ ይታመናል።

በርግጥ ለረጅም ዓመታት የሙስና ምንነትና ሊያስከትል የሚችለውን አገራዊ ችግር ማስገንዘብ የሚችሉ ብዛት ያላቸው መድረኮች ተካሄደዋል። 18 ዓመታትም የጸረ ሙስና ቀን በአገር ዓቀፍ ደረጃ ተከብሯል። መድረኮቹም ሆኑ ቀኑን በየዓመቱ ማክበሩ ግን ችግሩን በመከላከል ሂደት ውስጥ ይህ ነው የሚባል ለውጥ አላስገኘም፤እያስገኘም ነው ለማለት አያስደፍርም።

ለዚህም ይመስላል የዘንድሮ የጸረ ሙስና ቀን ‹‹ሙስናን መታገል በተግባ›› በሚል መሪ ቃል መከበሩ።በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ስር የሰደደውን ሙስና ለመዋጋት ቀን ከማክበር እና በመድረክ ከማውገዝ የዘለለ የተግባር እርምጃ ይሻል መባሉ።

በየትኛውም ሁኔታ የመንግስት አገልግሎት የሚፈልጉ ዜጎች በየአገልግሎት መስጫው እጅ መንሻ ይጠየቃሉ።ይህ አሰራር ነውር መሆኑ ቀርቶ ህጋዊ የሚመስልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ለመንግስታዊ ስራ በመንግስት ተቋም የተቀመጠ ሰራተኛ ለሚሰጠው መንግስታዊ አገልግሎት በግልፅ ገንዘብ መጠየቅና ያለ ፍርሃት መቀበል ከተለመደ ውሎ አድሯል፡፡

‹ምነው በእንቁላሉ ጊዜ በቀጣሁት ኖሮ› እንዳለቸው እናት ችግሩ በዚህ ደረጃ የአገር ህልውና ስጋት ከመሆኑ በፊት ተገቢውን ትኩረት ቢሰጠው ኖሮ እዚህ ደረጃ ላይ እንደማይደርስ ብዙዎች ይስማማሉ። ‹‹ሌቦቻችን›› እስኪጎረምሱና ጥርስ እስኪያወጡ ከመጠበቅ ሌብነትን ሲጀምሩ የሚቆነጥጥ አሰራር መዘርጋት ያስፈልግ እንደነበርም እንዲሁ።

‹‹በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ›› እንዲሉ አበው፤ ያለፉትን ሁለት ዓመታት በአገራችን ሰሜናዊ ክፍል ከተፈጠረው ግጭት ጋር ተያይዞ ሁኔታውን እንደ መልካም አጋጣሚ የተጠቀሙ ኃይሎች ችግሩ የከፋ ገጽታ እንዲኖረው አድርገውታል። አገር ባለቤት የሌላት ያህል ስርቆት አንገት የማያስደፋ የአደባባይ ተግባር ሆኖ ታይቷል።

በሁሉም የአገሪቱ ክፍል በሚባል ደረጃ ዜጎች መብቶቻችውን በእጅ መንሻ የሚያገኙበት ሁኔታ አስገዳጅ ሆኗል። በቅንነትና በታማኝነት ማገልገል እንደ ሞኝነት /አላዋቂነት/ የሚታይበት የአዕምሮ ውቅርም እየተፈጠረ ይገኛል።

በፀረ-ሙስና ኮሚሽን በኩል በተደጋጋሚ የሃብት ማስመዝገብ ቢደረግም ይህም ምዝገባ ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑት አካላት ይልቅ ምንም የሌለው የበታች ሠራተኛ ላይ ያተኮረ ከመሆኑ በላይ፤ በበላይ አመራሩ ረገድ ለመመዝገብ ዳተኝነት ቢኖርም የተመዘገበውም ሃብት ይፋ አለመደረጉ ሕብረተሰቡ የተደበቀ ሃብት እንዳይጠቁም ማነቆ ሆኖበታል።

በመንግስት በኩል ችግሩን ለመከላከል የተጀመረው ጥረት አገሪቱን አጋጥሟት ከነበረው የጸጥታ ችግር አንጻር በታሰበው መንገድ መሄድ ባይቻልም አሁን ላይ ሌባን ሌባ ብሎ መጥራት መጀመሩ፤ከዛም ባለፈ ብሄራዊ የጸረ-ሙስና ኮሚቴ በማቋቋም ችግሩን በዘመቻ ለመዋጋት እየሄደበት ያለው መንገድ የሚበረታታ ነው።

ይህንን ተከትሎ በወንጀሉ ተጠርጥረው ሆነ እጅ ከፍንጅ ተይዘው ሙሰኞች ለህግ እየቀረቡ ያለበት ሁኔታ የሚያበረታታ ቢሆንም ሙስና በአገሪቱ ካለበት ደረጃ አንጻር ገና ብዙ መስራት የሚጠይቅ እንደሚሆን ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ከሙስና የፀዳች አገር ለመፍጠር የግዴታ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ ማቅረብ ባይጠበቅ ባቸውም፤ የእሳቸውን ጥሪ ተከትሎ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የጸረ ሙስና ክልላዊ ኮሚቴ በሟቋቋም ወደ ሥራ መግባታቸው ጥሩ ጅምር ነው።

ታዲያ ይህ ጅምር ፍፃሜው ያምር ዘንድ ከለመድነው የጸረ ሙስና ያዝ ለቀቅ አሰራር ወጥተን ችግሩን አምርረን የምንዋጋበትንም ቁርጠኝነት መላበስ ይጠበቅብናል። በተለይም መላው ህዝባችን ከሙስና የጸዳች አገር የመፍጠሩ እውነታ የምንመኛትን የበለጸገች አገር ለመፍጠር ወሳኝ አቅም በመሆኑ በዘመቻው የሚኖረውን ተሳትፎ ማሳደግ ይጠበቅበታል።

ሌቦችን ከማጋለጥና ለፍርድ ከማቅረብ በተጓዳኝ ሙስናን የሚያበራታቱና ለችግሩ አቅም የሚፈጥሩ ማህበረሰባዊ ልምዶችንና አባባሎችን በመጠየፍ፤ ህዝብን በቅንነትና በታማኝነት ያገለገሉ ምስጉኖችን ማመስገን የሚያስችል አዲስ ሥርዓት መፍጠር፤ በዚህም የነገ ተመስጋኞችን ዛሬ ላይ መፍጠር የሚያስችል ዘር መዝራት ይጠበቅብናል፡፡

ይህን ለማድረግ ደግሞ የተወሰኑ ቡድኖች፣ ግለሰቦች፣ ተቋማት ወይንም የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻቸውን የሚወጡት ኃላፊነት አለመሆኑን በአግባቡ መረዳት ይገባል።ይልቁንም ሙስናን ለመዋጋት የተጀመረው ዘመቻ ስኬታማ እንዲሆን ሁሉም ዜጋ በየፊናው አገራዊ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ደማም (ሞሺ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## በአለም አደባባይ ግዝፈት ያገኘው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ፧

ባለፉት ሁለት አመታት በሀሰተኛ ፣ ሆን ተብሎ በተዛባና በተጣመመ መረጃ እና በሴራ ፓለቲካ የአገራችን ገጽታና ስም ክፉኛ ጠልሽቷል ፤ ጠፍቷል ። በዘር ማጥፋት ፣ በአስገድዶ መድፈር ፣ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ በሚፈጠር ወንጀል ፣ በጦር ወንጀል ፣ ሰብዓዊ ዕርዳታን እንደ ጦር መሳሪያ በመጠቀም ፤ አንድን ማህበረሰብ በመከበብና በማገት ፣ ወዘተረፈ በሚሉ የፈጠራ ክሶች ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከተላላኪዎቻቸው ፣ ከአለም ዓቀፍ ሚዲያውና ተቋማት ጋር በማበር ፣ በመቀናጀትና በመናበብ አገራችንን ምድራዊ ሲኦል አድርገዋታል ።

ለተከታታይ ሁለት አመታት በአለም ዓቀፍ ብዙኃን መገናኛዎች የሀሰተኛ ዜና ማሟሻ አድርገዋታል ። እውነትንና ፍትሕን ይዛ ሆን ተብሎ ሰሚና ተመልካች እንድታጣና እንድትገለል ተደርጓል ። ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይም በሀሰትና በፈጠራ ወሬ በአለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙኃን በሰላም የኖቤል አሸናፊው ጠቅላይ ሚንስትር ይሄን አደረገ ፣ ያን ፈጸመ እየተባለ ተሸሚጠዋል ፤ ስማቸው ጎድፏል ። የአረንጓዴ አሻራ እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ነው ከፍ ብሎ ገዝፎ የታየው ። ግሎባል ሆፕ ኮአሊሽንም በዚህ ሰዓት ለጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ እውቅና መስጠትና ሽልማት ማበርከት ሊያመጣ የሚችለውን ውርጅብኝ ንቆ በድፍረት ስለ አረንጓዴ አሻራ ለጠቅላይ ሚንስትሩ የአፍሪካ የላቀ አመራር ሽልማት የሰጠው ከሀሰተኛ መረጃውና ስም ማጠልሸቱ የገዘፈ ታላቅ ተግባር ስለሆነ ነው ።

ለአፍሪካ - አሜሪካ የመሪዎች 2ኛ ጉባኤ ዋሽንግተን ለተገኙት ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ ፤ ግሎባል ሆፕ ኮአሊሽን የተሰኘው ተቋም በዋሽንግተን ዲሲ ባዘጋጀው ልዩ ዝግጅት ላይ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄን አስመልክቶ ላሳዩት አመራር ‘የአፍሪካ የላቀ አመራር’ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።ኢትዮጵያ በ2011 ዓ.ም. የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርን ስታስጀምር፣ በአራት ዓመታት ውስጥ 20 ቢልዮን ችግኞችን ለመትከል ማቀዷ የሚታወስ ነው።

ኢትዮጵያ ከታቀደው ግብ አልፋ በመላ አገሪቱ 25 ቢልዮን ችግኞች በመትከል የአራት ዓመት ዕቅዷን አሳክታለች ይላል የ”አዲስ ዘመን”ዘገባ ። በዚህም የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እና ለደን መልሶ ልማት ላደረገችው አስተዋጽዖ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና አግኝታለች ። ለመሆኑ ጠቅላይ ሚንስትሩ እንደ አመራር ፣ ኢትዮጵያ እንደ አገርና ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ በአለም አደባባይ ሞገስና ክብር ያገኙት ምን ሰርተው ነው የሚለውን ለመገንዘብ 25 ቢሊየን ችግኝ መትከል ከአኅዝ በላይ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ።

በመንግስታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ፕሮግራም (ዩኤንኢፒ)አገራችን ኢትዮጵያን ለአየር ንብረት ለውጥ ክፉኛ ከተጋለጡ 10 አገራት አንዷ መሆኗን ይገልጣል ። መልሶ ኢትዮጵያውያን ግን የአየር ንብረት ለውጥን ከማያባብሱ ዜጎች ተርታ ይሰለፋሉ ይለናል ። ኢትዮጵያውያን በአማካኝ ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት ግሪንሀውስ ጋዝ 1.3 ሜትሪክ ቶን ወይም 1300 ኪግ ሲሆን በአንጻሩ የአሜሪካውያን 20ሺህ ኪግ ፤ ኩየታውያን ደግሞ 60 ሺህ ኪግ ግሪን ሀውስ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር ነው ። የቻይናና የሕንድማ አይነሳ ።

ይህ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ለከባቢ አየር ሙቀት መጨመር እዚህ ግባ የሚባል ድርሻ የሌላቸው አገራት የበለጸጉ አገራት ከኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ ወደ ከባቢ አየር በለቀቁት ከፍተኛ መጠን ያለው ግሪንሀውስ ጋዝ በተፈጠረ የአየር ንብረት ለውጥና የከባቢ አየር ሙቀት የተነሳ ለተደጋጋሚ የዝናብ ዕጥረት ፣ ለድርቅና ረሃብ ተዳርገዋል ።

አገራችን ከ1966 ዓም ጀምሮ በየአስር አመቱ ይጎበኛት የነበረው ድርቅ ከቅርብ አመታት ወዲህ በየአመቱ የሚከሰት ሁኗል ። አምና ፣ ካች አምናና ዘንድሮ እንኳ በቦረና ፣ በሱማሌና በደቡብ ክልል የተከሰተው ድርቅ በእንስሳትና በአርብቶ አደሩ ላይ ያስከተለውን ከፍተኛ ጉዳት አይተናል ። በመንግስት ርብርብ ድርቁ በሰዎች ላይ የከፋ ጉዳት ባያስከትልም የህልውናቸው መሠረት የሆኑ እንስሳቱ ላይ ግን የከፋ ጉዳት አድርሷል ። መጠኑ ቢለያይም እንደ 1966ቱ ፣ 77ቱና 87 ሰዎች በረሃብ እንደ ቅጠል አልረገፉም ።

በአናቱ የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱን የሚመጥን ምርት ባለመመረቱ ፤ በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለው ሰፊ ክፍተት ባለመጥበቡ ፤ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ህወሓት በከፈተው ጦርነትና እዚህም እዚያም በተከሰቱ ቀውሶች ፤ በኮቪድ 19ና ራሽያ ዩክሬንን በመውረሯ በተፈጠረ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ የተነሳ በከተሞች ሳይቀር ድምጽ አልባ ረሃብ ተከስቷል ። ኑሮው አልቀመስ ብሷል ።

አገራችን ዛሬ ለምትገኝበት ውስብስብ ችግር በርካታ ምክንያቶችን መደርደር ቢቻልም ዋነኞቹ ግን ሁለት ናቸው ። እነሱም አበክረን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አለመገንባታችን ፤ የተፈጥሮ ሃብታችንና የሰው ኃይላችንን በአግባቡ አቀናጅተንና አልምተን አለመጠቀማችን ናቸው ። ሰፊ ለም መሬት ፣ አመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ፣ የከርሰ ምድር ውሃ ፣ ዝናብና ወደ 123 ሚሊየን ከሚገመተው ሕዝብ 70 በመቶው ወጣት ስለሆነ ከምግብ ዋስትና አልፈን የተትረፈረፈ ምርት አምርተን ኢንድስትሪውን ፣ የአገልግሎት ዘርፉንና የውጭ ንግዱን ይዘን መነሳት እየቻልን ዛሬም እርዳታን የምንቀላውጥ መሆናችን አንገት ያስደፋል ።

ከለውጡ ወዲህ ግን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታውን ከግብርና ልማቱ ፣ ከአካባቢ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ጋር መሳ ለመሳ በማስኬድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያልተጠበቀ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ችለናል ። በ2025 ዓም ደግሞ የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቷን ወደ ዜሮ ለማውረድ ግብ ተጥሎ እየተሰራ ነው ። ባለፉት አራት አመታት 25 ቢሊየን ችግኞችን ተክላለች ። የኤሌክትሪክ ፍላጎቷንም ከታዳሽ ኃይል ማለትም ከግድብና ከንፋስ እያገኘች ሲሆን በቀጣይም ለማመንጨትም እየሰራች ትገኛለች ።

አገራችን በታሪኳ ከፈጸመቻቸው እየፈጸመ ቻቸው ካሉ ግዙፉን ፕሮጀክቶች ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጨምሮ አንድ ላይ ቢደመሩ የ” አረንጓዴ አሻራ “ን ያህል ክብደት አልሰጣቸውም ። የህዳሴውም ሆነ የሌሎች ታላላቅ ግድቦች ህልውና እንዲሁ 80 በመቶ አገሬው ኑሮ የተመሰረተበት ግብርና እጣ ፈንታ የሚወሰነው ዛሬ በትጋት በምንከውነው የአካባቢ ወይም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ነውና።

በቀደሙት ሶስት አመታት ከ18 ቢሊዮን በላይ አገር በቀል ችግኞችን ለዛውም ከሞላ ጎደል ስነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረጉ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች መትከል ተችሏል። ከተተከሉ ችግኞች መካከል እንደ አቡካዶ፣ ማንጎ፣ አፐል፣ ፓፓየ፣ ሙዝ እንዲሁም ቡና የመሳሰሉት ይገኙበታል። በአራቱም ዞር ከ90 ሚሊየን በላይ ሕዝብ በችግኝ ተከላው ተሳትፏል።

ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ችግኝ መትከል የአየር ንብረት ለውጥን ፣ የአለም ሙቀት መጨመርን ወይም የአካባቢ ጥበቃ ችግሮቻችን ለመፍታት የማይተካ ሚና አለው ። ድህነትን ፣ የምግብ ዋስትና ጉድለትን ፣ የምርታማነት ተግዳሮትን ፣ ድርቅን ፣ ረሃብን ፣ የዝናብ መቆራረጥንና መቅረት ፣ የውሃ እጥረትን ፣ የኑሮ ውድነትን ፣ በፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና በምርት አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት ፣ ስራ አጥነት ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን ፣ የጸጥታና የደህንነት ችግርን ፣ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር በማሳለጥ እና ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማለም መስፈንጠሪያ በመሆን ያገለግላል ። ለዚህ ነው ችግኝ ተከላን የችግሮቻችን ሁሉ መፍቻ ዋና ቁልፍ /ማስተር ኪይ/ ነውየምለው ።

በየአመቱ በአገራችን ከ92ሸህ ሔክታር መሬት በላይ ደን ይመነጠራል ፤ ይጨፈጨፋል ። በዚህ የተነሳ የደን ሽፋናችን ከ50 አመታት በፊት ከ35 በመቶ ከነበረበት ደረጃ ወደ ሶስት በመቶ አሽቆልቁሎ ነበር ። ለዝናብ እጥረት ፣ ለድርቅና ለከባቢ አየር ሙቀት ተዳረግን ። በየአመቱ ምርታችን ከ10 በመቶ በላይ መቀነስ ጀመረ ። በየአመቱ ከ35 እስከ 40 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይቀንሳል። ሆኖም ባለፉት አራት አመታትም ሆነ ከዚያ በፊት በተከናወኑ የችግኝ ተከላና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች የደን ሽፋኑን ወደ 17 በመቶ ማገገሙ ይበል የሚያሰኝ ነው።

የበጋ ስንዴ ፣ የኩታ ገጠም ግብርናን ፣ በተወሰነ ደረጃ ስነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረገ የቴክኖሎጂና የሜካናይዜሽን እገዛ ፣ የከርሰና የገጸ ውሃን አሟጦ የመጠቀም ፣ ፍራፍሬና አትክልት ላይ ለመስራት ፣ በተለይ ከአለፈው አመት ጀምሮ የከተማ ግብርና ትኩረት ማግኘቱ ፤ ሰሞኑን ደግሞ የሌማት ትሩፋት መጀመሩ ፤ በአርብቶ አደሩ የሚገኙ ጦም ያደሩ ሰፋፊ መሬቶችን በመስኖ ለማልማት አበረታች ጥረትና ርብርብ መደረጉ እና ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ለማስቀረት ግብ መጣሉ የአተያይ ለውጥ በማምጣቱ ተስፋ ያስቆረጠን ግን ደግሞ ብቸኛ ሊባል በሚችለው ግብርና ከምግብ ዋስትና ባሻገር ተስፋችንን እንድናድስ አድርጎናል። ለዚህ ነው ተስፋ ሰጭ ጅምር እውቅና መስጠት የሚያስፈልገው።

ችግሮቻችንን ሁሉ ፈታተን ፣ በታትነንና አገላብጠን ብንመረምራቸው አብዛኛዎቹ ከአንድ ቅርጫት የሚገኙ ናቸው ። የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ ካለመንከባከብ ፣ ካለመጠበቅና ካለማልማት ቅርጫት የአለም ሙቀት መጨመርን ተከትሎ በመጣ የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የተፈጥሮ ሀብታችን እየተጎሳቆለ በመምጣቱ ማለትም መሬታችን የተራቆተ ፣ ዝናባችን የአጠረና የተቆራረጠ በመሆኑ የከርሰና የገጸ ምድር ውሃችን በመመናመኑ ግብርናው ውጤታማ ሊሆን አልቻለም ።

በዚህ የተነሳ በግብርና ላይ የተመሰረተው የዜጋው ህይወት ፤ የአገሪቱ ልማት ችግር ላይ ወድቋል ። ይህ የሀብት ውስንነትን ፈጥሯል ። በዚህ የተነሳ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከአመት አመት እየተባባሱ መጡ ። እነዚህን ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ የተፈጥሮ ሀብታችን እንዲያገግም ሌት ተቀን መሰራት አለበት። መሬት ማገገም ፣ ውሃ መያዝ አለባት ።

ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው ችግኝ በመትከልና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በስፋት በማከናወን ነው።“ አረንጓዴ አሻራ “ የበሽታውን ምልክት ከማከም ይልቅ መነሻውን በማያዳግም ሁኔታ የመፈወስ አቅም እንዳለው በማመን ነው፤” አረንጓዴ አሻራ ! “ የእንቆቅልሾቻችን ሁሉ መፍቻ ዋና ቁልፍ (ማስተር ኪይ) የምለው ።

ለዚህም ነው 25 ቢሊየን ችግኞችን መትከል ከቁጥርና ከአኃዝ በላይ በየአመቱ የሚከሰተውን ድርቅ ፣ የበርሃማነት መስፋፋት ፣ የአፈር መከላት ፣ የዝናብ ዕጥረትና መቆራረጥ ፣ የገጸና የከርሰ ምድር ውሃ መቀነስን በመከላከል ፤ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር ከተመጽዋችነት የመላቀቅ የማሪያም መንገዳችን ፤ ሉዓላዊነታችን ሙሉኡ ማድረጊያችን ፤ የአገሪቱ ሁለንተናዊ ብልጽግና ማገርሽ መቀየሪያ ፤ አስተማማኝ ሰላም ማስፈኛችን ፤ እውነተኛ አንድነትና እርቅ ማረጋገጫችን ፤ ወዘተረፈ ስለሆነ አረንጓዴ አሻራ ከአኃዝ በላይ ከመሆኑ ባሻገር ጠቅላይ ሚንስትሩ እንዳሉትም እንደ አገርና ሕዝብ ብቸኛ መዳኛችን ነው ።

**አረንጓዴ አሻራ የሕዳሴያችን ዋልታና ማገር ነው !**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹ሰላም መስፈን አለበት ሲባል የሚጮህ ሰው ጤነኛ አዕምሮ ያለው አይደለም››

አቶ መረሳ ካሕሳይ
የእንድርታ ወረዳ የጊዜያዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት የቀድሞ ኃላፊ

አስቴር ኤልያስ

**የእንድርታ ወረዳ አስተዳደር ከ14 ዓመት በላይ የሕግ አማካሪ ሆነው አገልግለዋል፡፡ የለውጡ መንግስት የስልጣን መንበሩን ከያዘ በኋላ በፌዴራል መንግስትና በትግራይ ክልል አመራር መካከል በነበረው አለመግባባት የተፈጠረ መመሰቃቀል ቢኖርም በወቅቱ በወረዳዋ የጊዜያዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በወቅቱ የፌዴራሉ መንግስት የተናጠል ተኩስ አቁም ስምምነት አድርጎ ከክልሉ ሲወጣ በአገር መከላከያ ሰራዊት ታጅበው ከወጡት መካከል አቶ መረሳ ካህሳይ አንዱ ናቸው፡፡ አዲስ አበባ የመግባታቸውም ምስጢር ለሰላም በመታገል የሠላም አምባሳደር ለመሆን ነው፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ከሰላም ስምምነቱ ጋር በተያያዘና በሌሎች ወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል፡፡**



ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ በፌዴራል መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት እንዴት ተመለከቱት?**

**አቶ መረሳ፡-** በአሁኑ ወቅት በአገራችን እየነፈሰ ያለው የሠላም አየር ጥሩ ነው። የተደረገው የሰላም ስምምነት በእውነቱ ከሆነ ጥሩ ስንቅ እየሆነን ነው። እኔም በዚህ በሰላም ዙሪያ አስተያየት እንድሰጥ እድሉ ስለተሰጠኝ በጣም ደስ ብሎኛል።

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተካሄደው የሰላም ስምምነት ጠቃሚነቱ ለአገራችን ኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፤ ለቀጣናችን ብሎም ለአፍሪካና ለዓለም ጭምር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ይህ ሰላም ደግሞ አንዳንዶች እንደሚያጣጥሉት ሳይሆን በጣም ወሳኝ የሆነ ነው። በተለይም ቀደም ሲል በፌዴራል መንግስትና በሕወሓት መካከል ተፈጥሮ የነበረው ጦርነት በወንድማማቾች መካከል የተፈጠረ ጦርነት ነው፤ በታሪክ ደግሞ እንዲህ አይነቱ ነገር ሲያጋጥም ጎጂ ነው። በተባበረ ክንድ አገርን ማልማት ሲቻል፣ በተባበረ ክንድ የብልጽግናን ጉዞ ማስቀጠል ሲቻል እርስ በእርስ በመናቆር አሸናፊም ተሸናፊም የሌለው ጦርነት ማካሄድ አገር የሚጎዳ ወደ ጉስቁልናም የሚሰድ ነው። በተለይም ትውልድ ተጎድቷል። ጠላቶቻችን ከንዶቻቸው እንዲበረቱ እድል ሰጥተናቸዋል።

በፌዴራል መንግስትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ እና በኬንያ ናይሮቢ ላይ የተፈራረሙት የሰላም ስምምነት እኔም እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጣም ደስ አሰኝቶኛል። እንዲያውም ከአሁን በፊትም የትኛውም ሚዲያ ላይ ቀርቦ አስተያየት መስጠት የተለያየ ትርጓሜ ስለሚሰጥ በሚል ቀርቤ አስተያየት ሰጥቼ አላውቅም ነበር። የሰላሙ ጉዳይ ሲነሳ ግን አስተያየት እየሰጠሁ እገኛለሁ። ምክንያቱም የተደረሰበት የሰላም ስምምነት የፈጠረብኝ ደስታ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ላይ የተካሄደው የሰላም ስምምነት በኬንያም በተመሳሳይ ተካሂዷል፤ ይሁንና ይህ የሰላም ስምምነት ያልተዋጠላቸው አንዳንድ ዲያስፖራዊች አሉና ሰላሙን ዘላቂ ለማድረግ ምን ማድረግ ይገባል?**

**አቶ መረሳ፡-** ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የተቀመጡ ድንጋጌዎች አሉ። ተግባራዊ እንዲሆን ከማን ምን ይጠበቃል የሚለው ጉዳይ ተግባራዊ መሆን ሲችል ነው ሰላሙ ሊሰፍን የሚችለው። በሰላሙ ስምምነት ያሉ መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ በመጀመሪያ ሁሉም ሰው ከራሱ ጋር መታረቅ አለበት። ስለራሱም ቆም ብሎ ማሰብ አለበት። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሰላም አምባሳደር መሆን አለበት። ሰላም የሚጀምረው በመጀመሪያ ከራስ ነው።

መንግስትም ሆነ ፓርቲ ያልፋል። ሕዝብ ግን አያልፍም፤ አገር አያልፍም፤ ትውልድ አያልፍም። የሕወሓት አመራሮች ይህንን የሰላም ስምምነት ሳያመነቱ ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆን አለባቸው። የፌዴራል መንግስት ደግሞ ይህንን የሰላም ስምምነት ለማስፈጸም ለሰላም ጥቅም ያላቸውን ከግለሰብ እና ፖለቲከኞች ጀምሮ ኢትዮጵያን ወዳድ አካላትን አካቶ እንዲያግዙ በማድረግ ወደተግባር መግባት አለበት። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ሰው መተባበር አለበት። ሰርቶ መኖር የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው።

በቅርቡ በታሪካችን ያየነው እና የሰማነው የእነ ሶሪያንና ሌሎች አገራትን ሰላም በውስጣቸው ስላልነበረ አገር እንደ አገር ፈርሷል። እኛ ነገ አገራችን ከፈረሰች የት ነው የምንሄደው? ስለዚህ ሰላሙ ተግባራዊ እንዲሆን እያንዳንዱ ሰው ከግለሰብ ጀምሮ ለሰላም ጠበቃ መሆን አለበት። ስለሰላም መስበክ መቻል አለበት። ክፉ አስተሳሰብና አመለካከት በትውልድ መካከል መንገስ አይኖርበትም። የእያንዳንዱ ሰው ድርሻ ተደምሮ ለሰላም አስተዋጽዖ ይኖረዋል። ጥቂቶች የሰላም ተቃራኒ ሆነው በጦርነት የሚነግዱ ሰዎች እኛ የሰላም አምባሳደር ከሆንን በጦርነት ትርፍ እናገኛለን የሚሉ ሰዎች ባዷቸውን ይቀራሉ። ምንም የሚያመጡት ተጽዕኖ አይኖርም። ስለዚህ ሁሉም ሰው የሰላም አምባሳደር መሆን አለበት ባይ ነኝ።

ይህ ሰላም ከሁሉም በላይ የሚጥቅመው ለትግራይ ሕዝብ ነው። የትግራይ ሕዝብ ያለፈውን የጦርነት፣ የስቃዩን ጊዜ፣ ያጣውን ልማት፣ ያጣውን ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚ አስቦ ቀጣዩ ዘመን የሰላም እንዲሆንለት ተግቶ መስራት አለበት።ከሰላም ብዙ ማትረፍ ያስፈልጋል። በሌላ ትርክት ከሚጎዳዳው ወንድም እህቱ ጋር በሰላም አብሮ መኖር አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- በአርግጥ በፌዴራል መንግስት በኩል አስገዳጅ ሁኔታ ሆኖበት ወደጦርነት ቢገባም ጎን ለጎን ስለሰላሙ ጉዳይ ደፋ ቀና ማለቱ አልቀረም ነበር፤ እንዲያም ሆኖ የደረሰው ጉዳት እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኑ ወቅት ወደስምምነት ተመጥቷል። የሰላም ስምምነት ላይ በመደረሱም ወጣቱን ከሞት፤ ኢኮኖሚውንም ከውድቀት ይታደገዋልና እርስዎ ይህን እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ መረሳ፡-** የጦርነቱ መቆም ለኢትዮጵያውያኑም ሆነ የትግራይ ሕዝብም የኢትዮጵያ አንድ አካል ስለሆነ የሚያመጣው ጥቅም ምንድን ነው መባሉ በጣም ወሳኝ ነገር ነው። ሰላም ከሌለ መልማት ብሎ ነገር አይታሰብም። ማልማት ብቻ ሳይሆን ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስም ሆነ ውሎ መግባት አይሞከርም። ይህ ጦርነቱ ሲቆም በዋነኝነት የአገሪቱ ኢኮኖሚ በጣም ይረጋጋል። ሰዎች ባላቸው ተሰጥዖ፣ የስራ ድርሻና በተጨማሪ ባላቸው ኃላፊነት በአገራቸው በየትኛውም ጥግ ተዘዋውረው ሰርተው ቤተሰቦቻቸውን ማስተዳደር ይጀምራሉ። ኑሯቸውንም በሰከነ መንገድ ይመራሉ። ሌላው ደግሞ ማህበራዊ መስተጋብሩ ወደቀድሞው ይመለሳል። የዜጎች ማህበራዊ መስተጋብር ሲመለስ የመኖር መተማመን ላይ ይደረሳል። በጦርነት ወቅት የሚያልቀው ከሁሉም በላይ ወጣቱ ነው። ወጣቱ ደግሞ የልማት ዋነኛው አካል ነው። የነገውም የአገር ተስፋ በወጣቱ ላይ ነው። ስለዚህ ወጣቱን ከሞት መታደግ ነው።

ሌላው ነጥብ ጦርነት ሲኖር የውጭ አገር ሰው ወይም ደግሞ ኢትዮጵያውያኑ አሊያም ኢትዮጵያን የሚወዱ ሁሉ ከያሉበት አገር ወደአገራችን መጥተው ሰርተው ኢንቨስት ለማድረግ ይቸገራሉ። ይህ ማለት ደግሞ ዜጎቻችን የስራ እድል አያገኙም ማለት ነው። ስለዚህ ጦርነቱ ሲቆም ከተለያየ አገር ኢንቨስተሮች ወደአገራችን በመምጣት አገራችንን ማልማት ይችላሉ፤ በዚህ በኩል የሚገባቸው ስጋት አይኖርም። ይሄ መሆኑ ከፍተኛ የስራ ዕድል እንዲፈጠር ያደርጋል። በኤክስፖርት የውጪ ምንዛሬ ገቢ ያድጋል ።በዚህም ኢኮኖሚው መነቃቃት ይጀምራል።

**አዲስ ዘመን፡- የሰላም ስምምነቱ ከተካሄደ ሳምንታት የተቆጠሩ ቢሆንም እስካሁንም ያልተዋጠላቸው ኃይሎች አሉ። ከሰላም ይልቅ ጦርነት መፈለጋቸው የሚያመላክተው ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ መረሳ፡-** ይህ በጣም ወሳኝ ነጥብ ነው። እየገረመኝ ያለው ነገር ጦርነት መቆም አለበት፤ ሰላም መስፈን አለበት ሲባል የሚጮኽ ሰው ጤነኛ አዕምሮ ያለው አይደለም። እነዚህ አካላት ለትግራይ ሕዝብ ሲሉ አይደለም፤ ለትግራይ ብሎም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቆረቆር ሰላም የሚወድ አካል ነው እንጂ ሰላም ስለምን ተፈጠረ ብሎ ወደዓለም አደባባይ እየወጣ የጦርነት ነጋሪት መጎሰም ከዚህ በላይ ለኢትዮጵያም ሆነ ለትግራይ ሕዝብ ጠላት የለም። እኔ እነዚህን ሰዎች የማያቸው እንደጠላት ነው። ምክንያት ቢባል እነርሱ ራሳቸው በሰው አገር በሰላም ስላሉ ነው ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ የነበረው። ሰላም የማይኖር ከሆነ ራሱ ሰርተው መኖር አይችሉም ነበር። አሁን እነሱ በተመቻቸ ሁኔታ ላይ ናቸው። ጦርነት ምን ያህል አስከፊ ነው የሚለውን በቅርበት ሆነው አላዩም። በጦርነቱ እነሱም ሆኑ ቤተሰባቸው አልተሳተፉም። በአጠቃላይ የጦርነቱ ረመጥ አልገረፋቸውም። ስለዚህ በውጪ ሆነው የገቢ ምንጫቸው የሆነውን ጦርነት እንዲቀጥል ሰላም በአገር ላይ እንዳይሰፍን ይወተውታሉ።

ስለዚህ በውጭ አገርም ሆነ አገር ውስጥ ያለው ጦርነት ለምን ቆመ ብሎ አካኪ ዘራፍ እያለ ያለው ሰው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሆነ ለትግራይ ሕዝብ የሚቆረቆር ሳይሆን የሕዝብ ጠላት ነው። ከሰላም ትርፍ ይገኛል፤ ከሰላም ማደግ፤ ብሎም መበልጸግ ይገኛል። ከሰላም የሚገኘው ትርፍ የትየለሌ ነው። ከጦርነት የሚገኝ ጥቅም እንደሌለ እያወቁ የትግራይን ወጣት ለማስፈጀት በዓለም አደባባይ ክፉ የሆነ ሐሳብ እየሰነዘሩ አቤቱታ ማቅረብ በጣም ያሳዝናል። ከእነዚህ በላይ እኛ ኢትዮጵያውያን ጠላት አለን ብዬ አላስብም። የትግራይንም ሕዝብ አይወክሉም፤ እንዲህ ሲባል አንዳንድ ጤነኛ የሆኑ ዳያስፖራዎች የሉም ማለት አይደለም። ጤነኛ አስተሳሰብ ያላቸውና ለሰላሙ ዘብ የቆሙ አምባሳደሮችን እያመሰገንን በሌላ በኩል ደግሞ ስለምን ሰላም ተፈጠረ በሚል የሚናደዱ፤ የወንድማማቾችን ጦርነት የማያወግዙ፤ ይልቁኑ ጦርነቱ እንዲቀጥል የሚፈልጉ ሰዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ናቸው። እኔ እነዚህን

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ሰዎች የምገልጻቸው በዚህ መልኩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት ከሰላም ስምምነቱ ማግስት ጀምሮ የሰብዓዊ ድጋፍ ያለገደብ እንዲገባ ፣ መድኃኒት፣ ነዳጅ፣ ገንዘብ የመሳሰሉ ወደ ክልሉ እንዲደርስ ያሳሰሰ ጥረት እያደረገ ነው፤ የመሰረተ ልማት ጥገናውም ጎን ለጎን እየተካሄደ ነው። እንደ ክልሱ ተወላጅ ይህን የሚገልጹት እንዴት ነው?**

**አቶ መረሳ፡-** እንደሚታወቀው ከጦርነት የሚገኘው ትርፍ አለመልማት ነው፤ በሌላ በኩል ጦርነት መሰረተ ልማትን የሚያቀጭጭ ሲሆን፣ የሕዝቦችን ተባብሮ የመኖር እሴት ያሳጣል። ባለፉት ሁለት ዓመታት በተፈጠረው የእርስ በእርስ ጦርነት ኢትዮጵያን ጎድቷል፤ ትግራይን ደግሞ በልዩ ሁኔታ መሰረተ ልማቷን ጎድቷል።

ከዚህም የተነሳ ለሕዝቡ መሰረታዊ የሆነ ሰብዓዊ ድጋፍ እየተደረገለት ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ የስልክ፣ የመብራት ፣ የባንክ እና ሌሎች መሰረተ ልማቶች እየተጠገኑም አገልግሎት እየሰጡም ይገኛሉ። በጥቅሉ ለሰው ልጆች መሰረታዊ የሆኑ አቅርቦቶች ላይ የፌዴራል መንግስት በአግባቡ ትኩረት አድርጎ እየሰራበት ይገኛል። ይህ ድጋፍ ደግሞ ለሕዝቡ በወሳኝ ሰዓት የደረሰ አገልግሎት ነው። ቀደም ሲልም ቢሆን የፌዴራል መንግስት ሲሰራ የነበረው አካባቢው እንዲለማ ነው። አሁን ደግሞ ለሕዝቡ የሚያስፈልገው ሰብዓዊ ድጋፍም ሆነ ነፍስ አድን መድኃኒት ብሎም መሰረተ ልማትን በመጠገን ደረጃ የፌዴራል መንግስት ፈጣን የሆነ እንቅስቃሴ አድርጓል። አስፈላጊ የሆነውን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ አቅርቦቶችን በስፋት እያስገባ ይገኛል። ይሄ የሰብዓዊ ድጋፍ መቀጠል አለበት የሚል እምነት አለኝ። ሕዝቡ ደግሞ በእርግጠኝነት የሚናገረው ይህ ድጋፍ እየተደረገለት ወደቀድሞው ሥነ ልቦናውና የልማት እንቅስቃሴው እንደሚመለስ ጥርጥር የለኝም።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት ጦርነቱ ከመቀስቀሱ ከሁለት ዓመት በፊት በቻለው ሁሉ ሰላም እንዲሰፍን ስለሰላም ብዙ መስራቱ ይታወቃል፤ በመጨረሻም ሰምሮ በአፍሪካ ህብረት አሸማጋይነት የሰላም ስምምነቱ ተካሂዷል። የኢትዮጵያ መንግስት ለሰላም ያለውን ጽኑ አቋም እንዴት ተገነዘቡት?**

**አቶ መረሳ፡-** ይህ ያነሳሽው ጥያቄ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። የፌዴራል መንግስት ከመጀመሪያውም አንስቶ ከለውጥ ማግስት ጀምሮ ሕወሓት ሲያደርገው የነበረውን እንቅስቃሴ የፌዴራል መንግስት ‹ጦርነት አያወጣንም፤ የሚበጀን ሰላም ነው፤ እንነጋገር፤ በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን እንወያይ፤ እርስ በእርስ ብንናቆር ትርፍ የለውም። አሸናፊም ተሸናፊም ስለሌለ ሁሉም ይጎዳል› በማለት ለሰላም የነበረውን ቁርጠኝነት ያለመታከት ሲሰራበት ነበር። ይህ በእርግጥም በጣም መደነቅ ያለበት ነገር ነው። ይህንን ደግሞ በተግባር ማስመስከር ችሏል። ይህ አልበቃ ብሎ የአገር ሽማግሌ ተልኳል፤ ወደ ክልሉ ታዋቂ ሰዎች ሄደዋል። እናቶች ተንበርክከው ጦርነት አይበጀንም፤ እንነጋገር፤ እንወያይ፤ ተው ሲሉ አልቅሰዋል። ይሁንና ሰሚ አላገኙም፤ ጦርነቱ ተጀመረ። ከዚህም የተነሳ ወንድምና ወንድም ተገዳደለ። አሸናፊም ተሸናፊም የሚባል ነገር የለውም። የተጎዱት ኢትዮጵያውያኑ ናቸው። የተጎዳው የአገር ኢኮኖሚ ነው። የተጎዳው የዜጎች ስነልቡና ነው። በአጠቃለይ የተጎዳው ማንም ሳይሆን እኛው ራሳችን ነን። ጎጂውም ራሳችን ነን።

የፌዴራል መንግስት ከመጀመሪያው አንስቶ ለሰላም ብርቱ አቋም ነበረው። አሁንም ይህን እያስቀጠለ ነው ያለው። መጀመሪያም ቢሆን የፌዴራል መንግስት ለሰላም እጁን ሲዘረጋ ቆይቷል። በመጨረሻም በደቡብ አፍሪካ የተደረሰበት የሰላም ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን ለሰላም ያለው ቁርጠኝነትን በዓለም አደባባይ አስመስክሯል። ይህ የሚያሳየው መንግስታችን በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን በጀግንነት ብቻ ሳይሆን ለሰላምም አምባሳደር ሆነው መቆማቸውን ነው። ለሰላምም ጀግኖች መሆናችንን ያስመሰከረ ስለሆነ ይህ የሰላም



**የኢትዮጵያውያንን እድገት የማይወዱ አካላት ካሉ ለእነዚህ አካላት ያለኝ መልዕክት ለየትኛውም ፈተና ሸብረክ አንልም፤ አንወድቅምም የሚል ነው**

ጥሪ ከመጀመሪያው አንስቶ የመንግስትን ተነሳሽነት ያሳየና እያስቀጠለም ስለመሆኑ አመላካች ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እዚህ ያላችሁ የለውጡ አካልና የትግራይ ተወላጆች ከመንግስት ጋር መስራት የምትፈልጉት በምን ዓይነት አግባብ ነው?**

**አቶ መረሳ፡-** ይህ ጥያቄ እኛ የምንፈልገው ነገር ነው። እኛ ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ በኋላም ሆነ ከጦርነቱ በፊትም ጦርነት እንዳይኖር ታግለናል። እኔ የመንግስት ሰራተኛ ነኝ። የሕግ ሙያተኛ ነኝ። የእንድርታ ወረዳ አስተዳደር ከ14 ዓመት በላይ የሕግ አማካሪ ሆኜ ስሰራ ነበር። ከዚያ አገራዊ ለውጡ ከመጣ በኋላ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሳይሆን ለራስ ጥቅም ሲባል ብቻ ለውጡን ለመቀልበስ ብዙ ተሞክሮ ነበር። በሰሜኑ የተከሰተው ጦርነት ብቻ ሳይሆን በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ግጭት እንዲፈጠርም በሆድ አደሮች ሲጠነሰስ ባየን ወቅት ስንኮንን ነበር። የፌዴራል መንግስት ክልሉን ከተቆጣጠረ በኋላ የጊዜያዊ መስተዳድር ተቋቋመ። እኔም በተቋቋመው የጊዜያዊ መስተዳደር አንድ ጽህፈት ቤት በኃላፊነት እየመራሁ ቆየሁ። ስሥራ የቆየሁትም በእንድርታ ወረዳ የጊዜያዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሆኜ ነበር። በወቅቱ የፌዴራል መንግስት የተናጠል የተኩስ አቁም ስምምነት ከክልሉ ጋር አድርጎ ከክልሉ ሲወጣ በአገር መከላከያ ሰራዊት ታጅበን በ2013 ዓ.ም ከመቀሌ ተነስተን አዲስ አበባ ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም ገባን። አዲስ አበባ ስንመጣ መንግስታችንን አምነንና አገራችን ብለን ነው።

የመጣነው ልንታገል ነው። ለሰላም አምባሳደር ለመሆን ነው። ጦርነቱን ልናወግዝ ነው፤ ለትግራይ ሕዝብ የሚበጀው ጦርነት አይደለም። እኛ በወቅቱ የመጣነው ከፌዴራል መንግስት ጎን ቆመን የትግራይን ሕዝብ እናስተዳድራለን በሚል ነው። በዚህም ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ ቁርጠኞች ነን፤ አሁንም ደግሞ አገራችን የጋራ ናት። የሰሜኑ ሰው የሌለው ኢትዮጵያ ሙሉ አይሆንም። ስለዚህ ከፌዴራል መንግስት ጋር ቆመን ለመስራት ቁርጠኛ የሆንን በጣም በርካታ አመራሮች አለን። አሁንም ቢሆን ሕጋዊ በሆነ መልኩ ጥሪ እንዲደረግልን እንፈልጋለን። መደራጀት እንሻለን። የብልጽግናን ፖሊሲና ስትራቴጂ ማወቅ እንፈልጋለን። ከዚህ አኳያም መሰልጠን እንፈልጋለን። እንዲሁም መብቃት እንፈልጋለን። እዚህ አዲስ አበባ ከመጣን 16 ወራት ተቆጥረዋል፤ አንድም ቀን ግን ስልጠና አልወሰድንም። አንድም ቀን አንድ ሰው አናግሮን አያውቅም። ነገር ግን እየታገልን ያለነው ለአገራችን ነው። ለግለሰብ ብለን የምናኮርፈው ነገር የለም። አሁንም ቢሆን ቁርጠኞች ነን፤ ከመንግስታችን ብሎም ከኢትዮጵያውያኑ ጎን እንቆማለን። የሰላምም አምባሳደር ሆነን እንቀጥላለን። በቀጣይ ደግሞ አገራችንን ብሎም የትግራይን ሕዝብ ለማልማት አሁን ቁርጠኞች መሆናችንን በአጽንዖት መግለጽ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተግባር ምክር ቤት ከሰሞኑን በውጭ ለሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ክልሉን እንገንባ በሚል ጥሪ እንዳቀረበላቸው ተሰምቷል፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በውጭ አገር ላሉ የሰላሙ ደጋፊዎችም ሆነ ከሰላሙ በተቃራኒ ለቆሙ አካላት የሚያስተላልፉት መልዕክት ካልዎ?**

**አቶ መረሳ፡-** በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። በውጭ አገር ያሉ ዳያስፖራ፣ ፖለቲከኞች፣ ምሁራን እንዲሁም በተለያየ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች እንዳሉ እገነዘባለሁ። እነዚህ ለሰላም ጥብቅና የቆሙ፤ ኢትዮጵያ ሰው በፈለገችበት ጊዜ ከሰላም ጋር አብረው የቆሙ ሰዎችን በጣም ከልብ ማመስገን እፈልጋለሁ።

ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት አገራችን ያለችው በጣም ወሳኝ በሚባል ምዕራፍ ላይ ነው። በሰላሙ ጉዳይ ላይ በጥሩ ሁኔታ እየተጓዝን ስለሆነ እነዚህ ለሰላሙ ትብብር ያደረጉትን ሰዎች በጣም ማመስገን እፈልጋለሁ። በተለይ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተግባር ምክር ቤት ጥሪ አቅርቧል፤ እነዚህ ጥሪ የተደርገላቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚወዱ፤ የትግራይን ሕዝብ የሚወዱ የሰላም አምባሳደር የሆኑ ሰዎች ከዚህ ምክር ቤት ጋር በትጋት መስራት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ታሪካዊ ሒደት ነው። ለሰላም ዘብ ቆመው ከዚህ ምክር ቤት ጋር በጋራ ተባብረው የሰላሙ ጉዳይ ወደላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር ብሎም ሕዝባችንም ወደልማቱ እንዲገባ እንዲሁም ወደቀድሞ ትብብራችንና ማህበራዊ መስተጋብራችን እንድንመለስ አገራችን የያዘችው የብልጽግና ግስጋሴዋ በአግባቡ እንዲቀጥል አስፈላጊ የሚባለውን ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ለትግራይ ብሎም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስተላልፉት መልዕክት ይኖርዎት ይሆን?**

**አቶ መረሳ፡-** ኢትዮጵያ የራሷ ምርጥ የሆኑ እሴቶች ያሏት አገር ናት። በቅርቡ የእርስ በእርስ በሚያስብል ሁኔታ ወንድማማቾች ተጋጭተው እንደነበር የሚታወስ ነው። በዚህም ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት ከማለፉ በተጨማሪ የአገር ሀብትና ንብረት ወድሟል። ስለሆነም ኢትዮጵያውያን፣ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ከአገራችን ልማት ጎን እንዲቆሙ ጥሪ ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ሰላም እንዳትሆን የሚፍጨረጨሩ፤ በዓለም አደባባይ ስለአገራቸው ክፉ ነገር የሚያወሩና ከሰላም ተቃራኒ የቆሙ የተለያዩ ዳያስፖራዎች፣ ፖለቲከኞች፣ ምሁራን ብሎም በጥቅሉ የኢትዮጵያውያንን እድገት የማይወዱ አካላት ካሉ ለእነዚህ አካላት ያለኝ መልዕክት ለየትኛውም ፈተና ሸብረክ አንልም፤ አንወድቅምም የሚል ነው። ስለሆነም ሰላማችን ምሉዕ እንዲሆን ከጎናችን ብትቆሙና ብታግዙን ይበጃችኋል እላለሁ። ማንኛውም ሰው ስለጮኸ ከሰላማችን ዝንፍ አንልም። ስለዚህ ኢትዮጵያ ሰላም እንድትሆን የማይፈልግ ኃይል የዓለም ማኅብረሰብ፣ የዓለም መንግስታት አጽንዖት ሰጥተው እንዲያስቆሙልን እንፈልጋለን። ሰላም ለምን ተፈጠረ ብለው በዓለም አደባባይ ያልተገባ ቋንቋ በአገራቸው ላይ መናገር በራሱ ወንጀል ነው። በዓለም አደባባይ ሰላምን መስበክ እንጂ ጥላቻን መስበክና ጦርነት ለምን ቆመ ማለት የሕግ ጥሰት ነው። በመሆኑም የዓለም ማኅበረሰብ ይህንን አስተሳሰብ ሊያስቆምልን ይገባል። ኢትዮጵያን የሚወድ ማንኛውም አካል ኢትዮጵያውያን ለምን ሰላምን ፈጠሩ ብሎ የሚጮኸውን አካል ለማስቆም ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያ ብሎም የኢትዮጵያ ወዳጆች እነዚህን አካላት አደብ ግዙ ሊሏቸው ይገባል እላለሁ።

ለኢትዮጵያና ለትግራይ ሕዝብ ደግሞ ማስተላለፍ የምፈልገው አብረን የምንኖረው ሰላምና አገር ሲኖር ነው። ልጅ ወልደን የምንስመው፤ ዘርተንም የምናጭደው ሰላም ሲኖር ነውና ሁሉም ኢትዮጵያውያን ለሰላሙ አምባሳደር ሊሆኑ ይገባል። እያንዳንዱም የየራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል የሚል መልዕክት ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ መረሳ፡-** የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰላም ዙሪያ አስተያየት እንድሰጥ ላደረገልኝ ጥሪ እኔም በጣም በአክብሮት አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ተጨማሪ አቅም የሚሆነው ሲዳማ ባንክ

**አንተነህ ቸሬ**

በአንድ ሀገር የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ ሚና ካላቸው ባለድርሻ አካላት መካከል የፋይናንስ ተቋማት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ።እነዚህ ተቋማት በሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ውስጥ ካላቸው ሚና መካከል አንዱ ለኢንቨስትመንት ተግባራት የፋይናንስ ምንጭ መሆናቸው ነው።

የብድርና ቁጠባ ተቋማትን ጨምሮ ባንኮችና የመድን (Insurance) ድርጅቶች በአነስተኛም ሆነ በትልልቅ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች፣ ማኅበራትና ኩባንያዎች የስራ ማከናወኛ የገንዘብ ምንጮች እና የንብረት ዋስትናዎች ሆነው ይሰራሉ።ውጤታማ የኢንቨስትመንት ተግባራት አስተማማኝ የፋይናንስ አቅርቦት የሚፈልግ በመሆኑ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላው ዓለም ያሉ የኢንቨስትመንት ስራዎች ከእነዚህ የገንዘብ ተቋማት ተሳትፎ ውጭ የሚታሰቡ አይደሉም።

ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የበርካታ ዜጎችን ሕይወት በበጎ የለወጡት የብድርና ቁጠባ ተቋማት ለአነስተኛና መካከለኛ የኢንቨስትመንት ስራዎች ውጤታማነት የነበራቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አይዘነጋም።በኢትዮጵያ የብድር እና ቁጠባ ተቋማት ደንበኞች ቁጥር ከባንክ ደንበኞች ቁጥር በብዙ እጥፍ የላቀ ነው።ይህም ለአብዛኛው ህዝብ የብድር አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት እነዚህ ተቋማት እንደሆኑ አመላካች ነው።አንጋፋ የሚባሉት የብድርና ቁጠባ ተቋማት የፋይናንስ አቅማቸው ከብዙ አዳዲስ ባንኮች ጭምር የተሻለ ነው።ዛሬ በትልቅ ስምና አቅም የሚታወቁ ብዙ የኢንቨስትመንት ድርጅቶች መነሻቸው እነዚህ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ናቸው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የብድርና ቁጠባ (የማይክሮፋይናንስ) ተቋማት አስተማማኝና ፍትሐዊ በሆነ አሰራር እንዲሰሩና ሕዝባዊ ተዓማኒነት እንዲኖራቸው እንዲሁም ባንክ ሆነው ለመንቀሳቀስ የሚስችላቸው ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው  የሚያስችል መመሪያ ከሁለት ዓመታት በፊት ማውጣቱ ይታወሳል።የብድርና ቁጠባ ተቋማቱ ያላቸውን ግዙፍ የደንበኛና የፋይናንስ አቅም ትልልቅ በሆኑና የተሻለ ትርፍ ሊያመጡ በሚችሉ ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዲያውሉት የተዘጋጀው ይህ መመሪያ፤ ብዙ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ወደ ባንክ እንዲሸጋገሩና ወደ መደበኛ የባንክ ሥራ እንዲገቡ እያስቻለ ነው።

በዚሁ መመሪያ መሰረት ቀደም ሲል ‹‹ሲዳማ ማይክሮፋይናንስ ተቋም›› (Sidama Micro Finance Institution) በመባል የሚታወቀው የብድርና ቁጠባ ተቋም ‹‹ሲዳማ ባንክ አክሲዮን ማኅበር›› (Sidama Bank S.C.) ሆኖ በባንክነት ለመደራጀት በሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ አግኝቷል።ባንኩ 1 ሺ 988 ባለአክሲዮኖች ያሉት ሲሆን፤ የተፈረመ ካፒታሉ አንድ ቢሊዮን 447 ሚሊዮን ብር ነው።ከዚህ ውስጥ ከ583 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆነው ገንዘብ የተከፈለ ካፒታል ነው።

የሲዳማ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊቀ መንበር አቶ አብርሃም ማርሻሎ ባንኩ ከብሔራዊ ባንክ የሥራ ፈቃድ ማግኘቱን ተከትሎ በባንክ ዘርፍ ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚያስችሉትን የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እንዳከናወነ ይናገራሉ።አቶ አብርሃም በዚህ ረገድ ስለተከናወኑ ተግባራት ሲገልፁ ‹‹የባንኩ የውስጥ አሰራር የሚመራባቸውን መመሪያዎችን የማዘጋጀት፤ በብሔራዊ ባንክ መስፈርት መሰረት ውስጣዊ አደረጃጀቶችን የማሟላት፤ ከባንክ ዘርፉ ወቅታዊ እድገት ጋር የሚጣጣምና ባንኩን ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስችል የኮር ባንኪንግ ሶፍትዌር ግዢ ለመፈፀምና ባንኩ የሚመራበትን የአምስት ዓመታት ስትራቴጂካዊ እቅድ ለማዘጋጀት ቅድመ ዝግጅት ተግባራትን የማጠናቀቅ፤ የሰራተኞችን አቅም በስልጠና የመገንባትና ተቋሙን በብቁ ሰው ኃይል የማጠናከር፤ በመጀመሪያ ዙር የተሟላ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ 10 ቅርንጫፎችን በተለያዩ



አቶ ታደሰ ሐጢያ

**የባንኩን አገልግሎት የሚጠቀሙ በእርሻ፣ በሆቴልና በሌሎችም የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች አሉ።የተቋሙ በባንክ አሰራር መደራጀት ደግሞ ይህን አገልግሎት ለማስፋትና ለማዘመን ተጨማሪ እድልና አቅም ይፈጥራል።**

የሀገሪቱ አካባቢዎች የማዘጋጀት እንዲሁም በብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ ሂሳብን ጨምሮ የመጠባበቂያና የክፍያ ሂሳቦችን የመክፈት ተግባራት ተከናውነዋል›› ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ ባንኩ ባለፈው የበጀት ዓመት 142 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር ዓመታዊ ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ 177 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ ከእቅድ የበላይ የሆነ አፈፃፀም አስመዝግቧል።ይህም ካለፈው ዓመት የባንኩ አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር የ58 በመቶ ብልጫ እንዲኖረው አድርጓል።48 ሚሊዮን ብር ለማትረፍ አቅዶ 83 ሚሊዮን ብር በማትረፍ በባንኩ ታሪክ የተሻለ ውጤት ሆኖ ተመዝግቧል።165 ሚሊዮን ብር ተቀማጭ ገንዘብ በመሰብሰብም ከቀዳሚው ዓመት አፈፃፀም የ29 በመቶ እድገት አሳይቷል።

በብድር አቅርቦት ረገድ ደግሞ ባንኩ የሰጠውን ብድር በ86 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር (በ29 በመቶ) በማሳደግ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰጠውን ብድር 462 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ማድረስ ችሏል።‹‹የባንኩ የተበላሸ ብድር ምጣኔ ሦስት ነጥብ ስድስት በመቶ ሲሆን፤ ይህም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው የአምስት በመቶ ምጣኔ አንፃር ሲታይ የሲዳማ ባንክ የተበላሸ የብድር ምጣኔ ጤናማ እንደሆነ አመላካች ነው›› ይላሉ።

የሲዳማ ባንክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ታደሰ ሐጢያ ባንኩ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም በነበረበት ጊዜ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ሲያገለግል እንደነበር አስታውሰው፤ አገልግሎቱ አዋጭና ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ በብሔራዊ ባንክ ሕጋዊ ማዕቀፍ መሰረት ባንኩ ይህን አገልግሎቱን እንደሚቀጥልም ይናገራሉ።ባንኩ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል አንዱ የባንክ አገልግሎትን በገጠርና በከተማ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ መሆኑም ይህን አገልግሎቱን የማስቀጠል አካል ነው።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ተቋሙ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ አድርጓል። ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ የባንኩን አገልግሎት የሚጠቀሙ በእርሻ፣ በሆቴልና በሌሎችም የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች አሉ።የተቋሙ በባንክ አሰራር መደራጀት ደግሞ ይህን አገልግሎት ለማስፋትና ለማዘመን ተጨማሪ እድልና አቅም ይፈጥራል።

ተቋሙ ወደ ባንክ ሲሸጋገር ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን አነስተኛ መነሻ ካፒታል ለማሟላት የአክስዮን ሽያጭ ያከናወነ ሲሆን፣ የተፈረሙ አክሲዮኖች ተከፍለው እንዲጠናቀቁ በማድረግ ከመደበኛ የባንክ ስራዎች በተጨማሪ ዓለም አቀፍ የባንክ ስራዎችን ለማከናወንእየሰራ ይገኛል።‹‹ወደ ባንክ ስራ ስንገባ የጠንካራ የፋይናንስ አቅም ባለቤት መሆን ያስፈልጋል።አለበለዚያ አቅም ካላቸው ከሌሎች ባንኮች ጋር ለመወዳዳር አስቸጋሪ ይሆናል።ለትልልቅ የኢንቨስትመንት ስራዎች ብድር ማቅረብም ሆነ በፋይናንስ ገበያው ላይ ተፎካካሪ መሆን አይቻልም›› ይላሉ።ይህን ለማሳካትም የተፈረሙ አክሲዮኖች እንዲከፈሉና የኮርባንኪንግ (Core Banking) ስራን ለመጀመር የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተከናወኑ እንደሆነ አቶ ታደሰ ያስረዳሉ።

የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገበያ እንዲገቡ መፈቀዱ መልካም እድሎችና ፈተናዎች እንደሚኖሩት የሚገልጹት ዋና ስራ አስፈጻሚው፣ መልካም እድሎችን መጠቀም ከተቻለ ፈተናዎቹን መቀነስና ተወዳዳሪ መሆን እንደሚቻል ነው የተናገሩት።የባንኮቹ መግባት የሀገር ውስጥ ባንኮች ውድድሩን ለመቋቋም ራሳቸውን እንዲያጠናክሩ፣ በዚህም ተገልጋዩ ኅብረተሰብ ተጠቃሚ እንደሚሆን ይገልጻሉ። የኢትዮጵያ ባንኮች በካፒታል አቅምም ሆነ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ረገድ በሚጠበቅባቸውና ወቅቱ በሚፈልገው ልክ እየተንቀሳቀሱ አለመሆናቸውን ተናግረው፣ እነዚህን ክፍተቶች በማስተካከል ለውድድር መዘጋጀትና ለተገልጋዩ እርካታ መስራት እንዳለባቸው ይመክራሉ።ከዚህ አንፃር ሲዳማ ባንክ ትልቅ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶችን እንዲሁም ዳያስፖራውን ማሳተፍን ጨምሮ ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች ሁሉ ተጠቅሞ በባንክ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተወዳዳሪ ለመሆን ማቀዱን አቶ ታደሰ ገልፀዋል።

ሲዳማ ባንክ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚኖረውን አወንታዊ አስተዋፅኦ በተመለከተም አቶ ታደሰ ሲናገሩ ‹‹ገበያው አዋጭ በመሆኑ ባንኩ ለኢንቨስትመንት ስራዎች የፋይናንስ ምንጭ የመሆን አቅም አለው።ቀደም ሲልም የባንኩን አገልግሎት የሚጠቀሙ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች አሉ።ወደፊትም ባንኩ ይህን ተግባሩን በስፋት አጠናክሮ ይቀጥላል›› ብለዋል።

ሲዳማ ባንክ በማይክሮ ፋይናንስ ደረጃ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሲያገለግልና ለግለሰቦች እንዲሁም በአነስተኛና ጥቃቅን የንግድና ኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ ለተሰማሩ ማኅበራት የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል። ብዙ ግለሰቦችና ማኅበራትም በተቋሙ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ስራቸውን አሳድገው ዛሬ ትልልቅ ኢንቨስተሮች ለመሆን በቅተዋል።

የሲዳማ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዝደንት አቶ መስፍን ቂጤሳ እንደሚናገሩት፣ ተቋሙ በግል ንግድ ላይ ለተሰማሩ በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ባለውለታ ነው። እርሳቸውም ከባንኩ ጋር ያላቸው ደንበኝነት የቆየ መሆኑን አስታውሰው፤ ‹‹ከባንኩ የወሰድነው ብድር በጣም ጠቅሞናል፤ትርፋማ ሆነን እንድንሰራ አግዞናል›› በማለት የባንኩ የብድር አገልግሎት ለውጤታማነታቸው አጋዥ እንደሆናቸው አስረድተዋል።

‹‹አካባቢው በቡና ምርት የታወቀ ስለሆነ ባንኩም ለቡናው ዘርፍ ትልቅ ድጋፍ እያደረገ ነው›› የሚሉት አቶ መስፍን፤ ለቡና አብቃዮችና ነጋዴዎች እንዲሁም ለተደራጁ ማኅበራትም የፋይናንስ እድል እንደሚያመቻች ይገልፃሉ።በቀጣይም ከባንኩ ጋር ያላቸውን ደንበኝነት አጠናክረው፣ በይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ የተፈጠረውን መልካም እድል በመጠቀም ቡናን እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እቅድ እንዳላቸው ተናግረዋል።

‹‹ከዚህ ቀደም የነበረው የባንኮች ተደራሽነት ውስን ስለነበር ብድር ለማግኘት ችግሮች ነበሩ።ሲዳማ ባንክ ለኢንቨስትመንት ስራዎች ብድር በማቅረብ ጥሩ እድል ይፈጥራል፤ለልማት በተለይ ለኢንቨስትመንት ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ የሚገኝ ባንክ ነው።ጥሩ ተስፋ ያለው ባንክም ነው›› በማለት አቶ መስፍን ባንኩ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ስለሚኖረው አስተዋፅዖ ይናገራሉ።

በግል የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩት ወይዘሮ አየለች ዱካሞም የባንኩ ደንበኛ ናቸው።‹‹ቀደም ሲል የሲዳማ ማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ነበርኩ›› የሚሉት ወይዘሮ አየለች፤ ተቋሙ ባንክ ከሆነ በኃላ ከባንኩ ብድር መውሰዴ ስራዬን ሰፋ አድርጌ እንድሰራ አግዞኛል።ብዙ ሰው ከሲዳማ ባንክ ብድር እየወሰደ እየሰራ ነው፤እየተለወጠም ነው።ከባንክ ጋር መስራት ጥቅሙ ብዙ ነው፡፡›› ሲሉ ይገልጻሉ።ባንኩ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራዎች ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ትልቅ ድጋፍ ሲያደርግ እንደነበር አስታውሰው፤ ከባንኩ ብድር ወስደው ከአነስተኛ የንግድ ስራ ተነስተው ለትልቅ ደረጃ የበቁ ሰዎችን እንደሚያውቁም ነው የጠቀሱት።ወደፊትም ከባንኩ ጋር ብዙ ስራዎችን የመስራት እቅድ እንዳላቸው ተናግረዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# ትልቅ ትምህርት ረጅም መንገድ!

**አልማዝ አያሌው**

ረጃጅም ጉዞ በትራንስፖርት ውስጥ መጓዝ አሰልቺ ነው። ጉዞው ምቾት ባለው ሁኔታ ካልሆነ ደግሞ ይበልጥ አድካሚ ይሆናል። የመስታወት ጸሀይ፣ የመኪና ውስጥ ሙቀት አልፎ አልፎም ቢሆን የሚያጋጥም ግሳት ሀገር አቋራጭ መስመርን እንዳልመርጠው ያደርገኛል። ግን ደግሞ ወግ አዋቂ፣ ታሪክ ተራኪ ነገሮችን አጣፍጦ ነጋሪ ሰው ከጎን ካለ መንገዱ ‹ከምኔው!› እንድንል ያደርገናል። እናም እኔ ረጅሙን መንገድ ስጀምር በቅድሚያ የማስበው ጥሩ አጫዋች ከአጠገቤ እንዲኖር ነው። የያዝነውን ቆሎ በጋራ ቆርጠም፣ ውሃውንም ጎንጨት እያደረግን አብረን እንድንጓዝ ነው። ይሄው ምኞቴ ተሳክቶ የጀመርኩትን ረጅም መስመር በጨዋታ ተወጣሁት።

የጨዋታ ለዛ አዋቂ ናቸው ከጎኔ ያሉት አዛውንት። መቼም ዘንድሮ የሚወራ፣ የሚነሳ የሚወድቅ ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታ አይጠፋምና የፖለቲካ ወጋቸውን ጀመሩ። ጨዋታቸው የቀድሞውን ከአሁኑ እያዋሀዱ ደግሞ ለዛ ባለው ቋንቋቸው እያዋዙና ፈገግ እያሉ በመሆኑ ሙሉ ጆሮዬን አሳልፌ ሰጥቻለሁ። ደግሞ የራሳቸውን ብቻ አይደለም የሚያወሩት ተሳታፊ እንድሆንም የድሮውን ባይሆን የአሁኑን ታስታውሻለሽ አይደል እያሉ ጥያቄ ይጠይቁኛል ። የማውቀውን እመልሳለሁ፤ ግን ደግሞ አንዳንዱን የይለፈኝ አይነት ተወት አደርጋለሁ። እሳቸውም ይሄ የገባቸው ይመስላል ‹‹ሳታውቂው ቀርተሽ አይደለም! ነገሩ የዘንድሮ ሰዎች ነገር ቶሎ ትረሳላችሁ፤ ረስተሽው ካልሆነ ወይም ተወት አድርገሽ›› ይሉና ይቀጥላሉ። የራሳቸውን ጨዋታ የተዘለለውም መለስ ብለው እያስታወሱኝ ‹‹ይሄን አታውቂም?›› ይሉኛል።

‹‹የጊዜው ሰው ሁሉ ነገር አዲስ ይሆንበታል። ወይ አውቆ አያውቅ፤ ወይ ለማወቅ አይጠይቅ ብቻ ዝም ብሎ ታሪክ ማጥፋት፣ ክፋት ፣ ተንኮል፣ ልብላ ባይ ብቻ ምን...›› አሉና ቀጠሉ። በብዙ ሀገራዊ ጉዳዮች የተበሳጩ ይመስላሉ። ‹‹አሁን በሀገራችን አንዴ በብሄር፣ በጎሳ፣ በሀይማኖት እያልን፤ አንዴ በክልል ሌላ ጊዜ ሌላውን ነገር እያነሳን እንዲህ መጨካከን ነበረብን?›› ሲሉ ጠየቁ። መልስ አልሰጠሁም። ማለቴ በአንደበቴ እንጂ ጭንቅላቴን ነቅነቅ በማድረግ መመለስ አላቆምኩም።

‹‹አንድ ጨዋታ ላጫውትሽ›› ብለው ጉሮሯቸውን ለንግግር እንዲመቻቸው ሳል ሳል አደረጉ። ‹‹ታሪኩን በደንብ አድምጪ›› ሲሉም ትኩረት እንድሰጠው ጋበዙኝ። ፊቴን ወደፊታቸው መለስ ከማድረጌ ትረካውን ቀጠሉ። ‹‹ሶስት ሰዎች ናቸው፤ እንዲህ እንደእኛ ረጅም መንገድ የወጡ። የፈለጉበት ቦታ ሳይደርሱ የመሸባቸው ናቸው። መንገዱን በጭለማው ቀጥለው ቢሄዱ አውሬውን ፈሩ፤ ረጅም ጉዞ አድርገዋልና ርቧቸዋል፤ ውሃ ጥሙም ፈተኗቸዋል፤ እናም ‹የመሸበት መንገደኛ እንበል› ሲሉ ተመካከሩ። እንደምታውቂው ድሮ መንገደኛ መንገድ ሲጓዝ ውሎ ሲመሸበት፤ ወይም የቆሎ ተማሪ ወደ አንዱ ገዳም ሲጓዝ ውሎ ሲመሸበት ‹የደከመው ...የራበው መንገደኛ› ብሎ ምጸዋት ይጠይቃል። አሳዳሪ ይለምናል ። ያን ጊዜ ባለቤቶቹ ይወጡና ‹ማነህ? ከየት መጥተህ ነው?› ብለው ጠይቀው ለእግሩ ውሃ፣ ለረሀቡ ማስታገሻ ምግብና የሚጠጣ ውሃ ሰጥተው፣ መኝታ መደብ አንጥፈው ያስተናግዳሉ። እንግዳውም በሚገባ ተስተናግዶ ማልዳ ተነስቶ ስላደረጉለት መልካም ነገር አመስግኖና መርቆ መንገዱን ይቀጥላል።›› በማለት በላብ የወረዛ ፊታቸውን በእጃቸው መዳፍ ዳሰስ አደረጉት።

‹‹ይሄ በሁሉም የሀገራችን ክፍል የተለመደ ነው። የማን ዘር ነህ? የትኛው ሀይማኖት ተከታይ ነህ? ብሎ ጥየቃ የለም። ብቻ ሰው የተቸገረ ሰው መሆኑን ከተረጋገጠ በቂ ነው። እንግዳ ደራሽ

> **የኖርንበትን መልካምን ታሪክ ማስታወስ ያስፈልጋል። የማይጠቅመንን ትተን የሚሆነን ይዘን ሀገራችንን ሀገር ማድረግ እንደ ህዝብም ታሪካችንን ማስቀጠል ይሻለናል**

ተብሎ በክብር ተስተናግዶ ይሸኛል። እነዚያም ሶስት ሰዎች ይሄን ያውቁ ነበርና ሁሎችም አንድ ቦታ ከመግባት ብለው ‹አንተ ሂድና እዚህ ጠይቅ› ይሉታል፤ ‹ማነህ ካሉኝ ማነኝ ልበል?› ይላቸዋል። ሁሉም የመሰላቸውን ነገሩት። አዋጪ ምክር ያሉትን ለገሱት። እርሱ ግን ሓይ በጣም አድርገው እንዲያከብሩኝ፣ እንዲፈሩኝ የምላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉልኝ እግዚአብሄር ነኝ እላቸዋለሁ› ብሎ ወደፊት ሄደ። እንዳለው ለተጠየቀው ጥያቄ ‹እግዚአብሄር ነኝ› ብሎ መለሰላቸው ። ሰዎቹ ግን እጅግ በጣም ተናደዱ፤ ፊታቸው ሁሉ በአንዴ ተለዋወጠ። ያን ግዜ እንግዳውም ደነገጠ። ‹ጌታን ተፈታተንከው› ብለው ይሆን ብሎ የሚሆነውን ሁሉ በጺጋ መጠበቁን ቀጠለ።

የቤቱ ጌታ ተናደውና ተበሳጭተው ‹በሀገር ላይ ይሄ ሁሉ ደም ሲፈስ ያሁሉ ነፍስ ሲጠፋ ልጅ በአባቱ ወንድም በወንድሙ ላይ ሲጨካከን ስንጠራህ! ስንጮህ! የት ነበርክ ? አሁን ብቅ ያልከው። አንተማ የፍጥረትህን ድምጽ የማትሰማ በመሆንህ አናሳድርህም› ብለው መለሱት። እሱም ወደ ጓደኞቹ ሄዶ የሆነውን ሁሉ በጣም አዝኖ ነገራቸው ። እንዴት እግዜአብሄር ነኝ ላላቸው ይሄ ሁሉ ባይሆን ወደፊት ስቃያችንን ተመልከት፤ ጥሪያችንን ተቀበል ብለው ማለት ሲገባቸው ብሎ መሬቱን እየቆረቆረ የተሰማውን ሁሉ ገለጸ።

ሌላው ደግሞ ቀበል አድርጎ እኔ ደግሞ ሌላኛው ቤት ሄጄ እድሌን ልሞክር አለ። እንዴት በዚህ ጨለማ አውሬ እንዲበላን እንፈቅዳለን ብሎ ተነሳ። ‹ማነህ ስትባል ማነኝ ትላለህ ? › አሉት እሱም አውጥቶ አውርዶ ከምንም በላይ ጥሩ ነገር ‹‹ፍቅር›› ነው። ፍርቅር ነኝ ብዬ እላቸዋለሁ አለ። የመረጠውን የገበሬ ቤት አንኳኳ። ብቅ ብለው ማነው አሉ ። እኔ ነኝ የመሸብኝ መንገደኛ አሳድሩኝ ብዬ እየለመንኩ ነው አለ። እንደተለመደው ጥያቄ ቀረበለት፤ እሱም ፍቅር መሆኑን ነገራቸው። በአጋጣሚ ብቅ ብለው የጠየቁት የቤቱ አባወራ ናቸው።

እሳቸው ከሚስታቸው ጋር በነበረባቸው መጋጨት በፍቅር ማጣት ተጣልተው ከተለያየ አጭር ጊዜያቸው ነው። ቤተሰባቸው ፍቅር አጥቶ ጸብ በቤቱ ነግሶ ኑሮው ሁሉ ተደበላልቆ ባቸዋል ። እኚህ ሰው ‹‹ፍቅር›› የሚለውን ቃል ፈጽሞ መስማት አይፈልጉም ፤እንዳው ቢሆንላቸው በጉልበት፣ በሀይል፣ በደሉኝ አስከፉኝ ቤቴን በጠበጡ ያሉትን ሁሉ መበቀል የሚፈልጉ ናቸው። እናም ውጣ ከቤቴ አንተን የማሳድርበት ምክንያት የለኝም ብለው አመናጭቀው መለሱት ። እሱም እያዘነና እየተከዘ ወደ ጓደኞቹ ሄዶ የሆነው ሁሉ ነገራቸው። ሁሉም አዘኑ የአንዳችንም ሳይሳካ እዚሁ አውሬ ሊበላን ነው ብለው ተጨነቁ ።

ሶስተኛው ሰው እኔ ደግሞ እድሌን ልሞክር ብሎ ተነሳ ፤ሁሉም በጸሎት ሸኙት። እርሱም ሁለቱ ያላንኳኩት ቤት ሄዶ የመሸበት መንገደኛ አለ። ማነህ የሚለው የተለመደው ጥያቄ ቀረበለት። እሱም መላዕከ ሞት መሆኑን ተናግሮ መንገድ እየሄደ መሽቶበት መሆኑን አስረዳ ፤እንድታሳድሩኝ ብዬ ነው ብሎ ጠየቀ። የቤቱ ጌታ ከመቀመጫቸው ተነሱ። ግባ ብለው እግሩ ላይ ወደቁ ።አንተማ ሁሉን እኩል የምታደርግ፣ ደሀ ከሀብታም የማትለይ ፣ ልጅ አዋቂ ፣ ምሁር መሀይም የማትመርጥ ፣ የእጅ መንሻ ምናምን የማትል ሀቀኛ አንተን ያላሳደርን ማንን እናሳድራለን ። ግባ ከእልፍኙ ብለው የሚበላ የሚጠጣውን የሚተኛበትን ሁሉ ለደከመው እግሩ የሙቅ ውሀ ጭምር ሰጥተው አስተናገዱት። እሱም በጥሩ መስተንግዶ ተስተናግዶና አድሮ ሲነጋጋ ስንቅ ተቋጥሮለት ከአደረበት ወጣ አሉ፤ ብለው በጣፋጭ አንደበታቸው ተረቱን ነገሩኝ። ትልቅ ሰው ተረቴን መልሱ አይባልም እንጂ ተረቴን መልሱ ብላቸው ደስ ባለኝ ነበር።

‹‹ይሄ ተረት አሁን ገብቶሻል›› ሲሉ ፈጠን ብለው መልስ እየሻቱ ጥያቄ አቀረቡ ። እናም ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ አፍ አፌን ተመለከቱ ። የመሰለኝን ነገርኳቸው ስህተት አላሉም ራሳቸውን ነቀነቁ። ትክክል ነኝ ብዬ ደስ አለኝ። እሳቸው ግን ይሄንን ሁሉ ወግ ያመጡት ከሀገራዊ ሁኔታው ጋር አገናኝተው ነው። በሀገራችን አሁን ያለው ሁኔታ ከምንጠብቀውና ከምንፈልገው የተለየ ነው። ፍቅር እየጠፋ ጸብ እየነገሰ፤ ርህራሄ እየጠፋ ጭካኔ እያየለ ነው። መረዳዳት ሳይሆን መቀማማት የበዛበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ሹመኛው ማንን ላገልግል ሳይሆን እንዴት ልገልገል ብሎ ነው የሚያስበው። ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል ብሎ ነው የሚነሳው፤ እኔን ምረጡ አገለግላችሁለሁ ብሎ ገብቶ ህዝብ ያስለቅሳል አገልግሎት በገንዘብ ግዛ ይላል።... ቀጠሉ ድሮም እኮ ጉቦ አለ፤ እጅ መነሻ ።አሁን ያ አይደለም አድጎ ገዝፎ ንጥቂያ ሆኗል። እኛ እንኑር ሀገር ይጥፋ ነው ነገሩ ሁሉ። መሬቱን ፣ ሀብቱን፣ ፕሮጀክቱን ሁሉ ዘራፊ እንጂ አልሚ አልገጠመውም። ብቻ አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሰናል።

ፈሪሀ እግዚአብሄር ጠፍቷል። የሀይማኖት አባት ፣ የጎሳ መሪ ፣ታላቅ ታናሽ መባባሉ ተረስቷል። ማን ማንን አዳምጦ! ብቻ ህገወጥነት ሰፍቷል። እናም ሁሉም የመረጠው፣ መላከ ሞትን ሆኗል። ይሄ ያልኩሽ የነገርኩሽ ሁሉ ተረት ተረት አይደለም፤ የእኛው የኢትዮጵያውያን አሁናዊ ገጽታ ነው። ባይጥምሽም...። ሁሉ እኛኑ የሚገልጽ ነው። ኢትዮጵያውያን ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ሁላችንም በመጠፋፋት አዙሪት ውስጥ ነን። ፖለቲካው ስልጣኔው ሁሉ የሚያፋቅር የሚያዋድድ ሳይሆን ቂም ቁርሾ መወጣጫ ሆኗል። በህይወት ባሉት ብቻ ሳይሆን በስም ባሉት ሁሉ መከራ ተቀበሉ በዝቷል›› እያሉ የተሰማቸውን ሁሉ ዘረዘሩ። መራር ቢሆንም በዘመናችሁ በዘመናችን የምናየው የምንቀምሰው እውነት ስለሆነ ተቀበይ አሉ። ይህን መከራከር አልፈለኩም። ደጋግሜ ራሴን ነቀነቅኩ።

እርሳቸው ግን አላቆሙም ‹‹አይተሽ የለ ያን ሰሞን ያ ሸኔ የምትሉት ጨካኝ በወለጋ አካባቢ የፈጸመውን ግፍ። የጨረሳቸውን ህጻናት ሴቶች አይተሽ የለ!? ››ሲሉ ጠየቁ፤ መልስ ሲያጡ መቼም ሰምተሻል ብለው ለጥያቄው ራሳቸው መልስ ሰጡ ። እሱማ ብዙ ሰምተናል። የሰው ልጆች ሞት ቁጥር እስኪመስለን ድረስ አድምጠናል። ኦሮሞው፣ አማራው፣ ሙስሊሙ፣ ክርስቲያኑ ሳይለዩ አልቀው አንድ ላይ ተቀብረው ሰምተናል። አሰቃቂ የሚባሉ ግድያዎችን አይተን ይሄ በኢትዮጵያ ውስጥ የሀይማኖተኞች መኖሪያ ሀገር በምትባለው ሀገራችን በራሳችን ወገኖቻ የሆነ ነው ብለን እግዚኦ ብለናል።

አሁንም ግን ገና አልተማርንም ። አሁንም ገና ፈጣሪን ፍጡሩን እያጠፉን መሆናችን ገብቶን ፈጣሪ ይፈርድብናል ብለን ከጥፋት አልተመለስንም። አሁን ከሁሉም ነገር በላይ ፍቅር ይበልጥ ጥፋትን በይቅርታ፤ ጸብን በፍቅር እንተካው ብለን ለንሰሀ አልተዘጋጀንም። አሁንም በቃን ብለን በህብረት በአንድነት ለመኖር አልተነሳሳንም ።አሁንም በውስጥ ክፋትን አዳፍነን ነው ያለነው። ትንሽ ነገር ብቅ ስትል የተዳፈነውን ረመጥ ገለጥለጥ ከማድረግ አልቦዘንም። ዛሬም እናስገባው እንጋብዘው እናክብረው ብለን ያለነው መላከ ሞትን ነው።

ግን ደግሞ ቆም ብሎ ማሰብ ይገባል። የኖርንበትን ታሪክ ማስታወስ ያስፈልጋል። የማይጠቅመንን ትተን የሚሆነን ይዘን ሀገራችንን ሀገር ማድረግ እንደ ህዝብም ታሪካችንን ማስቀጠል ይሻለናል። ይሄንን ማን ይጀምር? ይሄንን ማን ያድርግ? ይሄንን ማን ያዳምጥ? በይ እንግዲህ ለአንቺም እንደ አቅምሽ የቤት ስራ ሰጥቼሻለሁ። ሁሉም የአቅሙን ከሰራ በሆነውና በሚሆነው ነገር ተጸጽቶ ከተመለሰ መጥፎው ሁሉ በጥሩ ይገለጣል። እኔ አበቃሁ፤ አቦ እንዴት አደከምሽን፤ የመንገዱን መርዘም ወሬው አሳጠረው እንጂ መቼም ይደክመን ነበር›› ብለው በረጅሙ የድካም አየር ተነፈሱ። በእውነት ትልቅ መልዕክት ትልቅም ትምህርት ረጅም መንገድ ከጥሩ ማወራረጃ ጋር እንዲህ የጣፈጠና ያጠረ ነው። ኬር.....ኬር ይሁን ብለን ተሰነባበትን።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# በአገራቸው የማይታወቁት የኢትዮጵያ የሙዚቃ ቅኝቶች

**ዋለልኝ አየለ**

ባለፈው ጥቅምት ወር ስለኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ አውርተን ነበር። ባለፈው ሳምንት ደግሞ ዘመኑ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ መሰረት ያደረገ የሙዚቃ መተግበሪያን በተመለከተ አስነብበናችኋል።

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ የራሷ ማንነት አላት ብለን ለመናገር ከምንጠቅሳቸው ነገሮች አንዱ ሙዚቃ ነው። አገር በቀል የሙዚቃ መሳሪያዎችና አገር በቀል የዜማ አይነቶች አሉን። መጠሪያቸውም አገር በቀል ነው። ስለዚህ እነዚህን የራሳችን የሆኑ ነገሮችን ማስተዋወቅ አለብን።

ከጥንቱ የሙዚቃ ታሪካችን ተነስተን አሁን ያለው ዘመናዊ የሙዚቃ መተግበሪያ ላይ ደርሰናል። በዚህ ሁሉ የሙዚቃ ሂደት ውስጥ ግን አንድ ልብ የማንለው ነገር አለ። ይሄውም ረቂቅ የሆነው የቅኝት አይነቶች ነው። ምናልባትም የሙዚቃ ባለሙያ ካልሆነ በስተቀር ተራው ዜጋ ልብ ላይለው ይችላል። አንድን ዘፈን አሰምተን ‹‹ምን የሚባል ቅኝት ነው?›› ተብሎ ቢጠየቅ ምናልባትም ትዝታ ብቻ ይመስለኛል ብዙ መላሽ የሚያገኘው።

ከአራት ይሁን አምስት ዓመት በፊት በቴሌቭዥን ከሰማሁት አንድ ትዝብት ልነሳና ወደ ዋናው ጉዳይ ልሂድ።

በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እሁድ መዝናኛ ፕሮግራም ላይ ጋዜጠኛው ወጣቶችን እያስቆመ ይጠይቃል። ጥያቄውም ‹‹አራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች›› የሚባሉትን እንዲነግሩት ነበር። ወጣቶቹ እንኳን የቅኝቶችን ስም ‹‹አራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች›› የሚባሉ መኖራቸውንም የሚያውቁ አይመስሉም። ትንሽ ሞከሩ የተባሉት ደግሞ የእስክስታ ስሞችን ነው የተናገሩት።

አራቱን የሙዚቃ ቅኝቶች ‹‹አናውቃቸውም!›› ያሉት ወጣቶች ናቸው። ወጣቶች ማለት ደግሞ ለሙዚቃ ያላቸው ፍቅር ግልጽ ነው። ግልጽ የሚሆነው ግን ለሮክ፣ ብሉስ፣ ቻቻቻ፣ ባቻቻ... ለሚባሉት የውጭ ሙዚቃዎች ነው። በታክሲ ውስጥም ይሁን በሥራ ቦታ አብዛኛው ወጣት በጆሮ ማዳመጫ ጆሮውን ደፍኖ ነው የምናየው። ኤፍ ኤም ሬዲዮ እየሰሙ አይደለም። ‹‹እንዴት አወቅክ›› አይባልም። የአንዳንዶቹ እኮ በጆሮ ማዳመጫ ይሁን እንጂ እንኳን ከአጠገባቸው ላለ ሰው አልፎም እስከሚሰማ ነው የሚጮኸው። እነዚህ ወጣቶች ‹‹አራቱን የሙዚቃ ቅኝቶች ‹‹አናውቃቸውም›› ብለዋል። ጠንቀቀው የሚያውቁ ቢኖሩም እያወራን ያለነው ስለማያውቁት ነው።

በወጣቶቹ አራቱን የሙዚቃ ቅኝቶች ‹‹አናውቃቸውም›› ማለት የተገረመ ካለ ሌላ የባሰ አስገራሚ ነገር ይጨመርለታል። በአንድ የሙዚቃ ውይይት ላይ እንደሰማሁት፤ በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት(ልብ በሉ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ነው) በትልቅ ኃላፊነት ላይ የሚገኙትን አንድ ጋዜጠኛ ስለአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች ይጠይቃቸዋል። ሰውየው ‹‹የሙዚቃ ቅኝቶች በጣም ብዙ ናቸው›› አሉ። ጋዜጠኛው ከአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች ውጭ ሰምቶ ስለማያውቅ አዲስ ሆኖበት ብዛታቸውን ደጋግሞ ጠየቀ። ሰውየው ለካ አያውቋቸውም። በተደጋጋሚ ‹‹በጣም ብዙ ናቸው›› እያሉ መለሱ። እንግዲህ እርሳቸው የመሰላቸው በአገሪቱ ውስጥ ከሰማንያ ምናምን በላይ ብሄር ብሄረሰቦች ስላሉ የሙዚቃ ቅኝቶችንም ከሰማንያ በላይ ይሆናሉ ብለው የገመቱ ይመስላል።

እርግጥ ነው ከአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች ውጭ አሉ የሚሉ አዳዲስ ሀሳቦች እየመጡ ነው። ‹‹ፊላና ሌሎች ሙዚቃዊ ጥበባት በጋርዱላ ዲራሼ›› የተሰኘ በ2012 ዓ.ም የታተመ የፍሬው ተስፋዬ መጽሐፍ በደቡብ ኢትዮጵያ ስለሚገኙ ሙዚቃዎች ይነግረናል። በጥናት አዳዲስ ነገሮችን ማግኘት የተለመደ ነው። ዳሩ ግን የነበሩትን እንኳን አለማወቅ ደግሞ አገርን አለማወቅ ነው።

እንግዲህ የአንድ አንጋፋ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ኃላፊ እንዲህ ካሉ በሌሎች መፍረድ አይቻልም ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናቶች ሲሰሩ፣ የመገናኛ ብዙኃን ፕሮግራም ሲሰሩበት እምብዛም አይስተዋልም። ሙዚቃ ቀላል ነገር ሆኖ ነው እንዳይባል በውጭው ዓለምም ሆነ በአገር ውስጥ ሰዎች ለሙዚቃ ምን እንደሚሆኑ በግልጽ



እየታየ ነው። የሙዚቃ ኢንዱስትሪም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ነው። ይህ የሆነው ግን በውጭው ዓለም እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም። ለዓለም ምሳሌ መሆን የሚችሉ አገር በቀል የሙዚቃ ቅኝቶች እያላት ከወጣት እስከ አዋቂ የውጭውን አድናቂ ሆኗል።

ለመሆኑ አራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች እነማን ናቸው? ከአራቱ ውጭ ሌሎች የአገራችን የሙዚቃ ቅኝቶች እንዳሉ ከዚህ በፊት በዚሁ ጋዜጣ አስነብበናል። ዛሬ ስለአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች ነው። በእነዚህ ላይ ጥናትስ ተሰርቶ ያውቅ ይሆን? እስኪ ለዛሬ በምሁራን የተሰሩ ሁለት ጥናቶችን ዋቢ አድርገን ስለአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች እናውራ።

በወሎ ዩኒቨርሲቲ የባህልና ኪነ ጥበብ ዳይሬክተር ጽህፈት ቤት የወሎ ዩኒቨርሲቲ የሙዚቃና ኪሮግራፊ አስተባባሪ አቶ ፋሲል መንግስቱ ‹‹የአራቱ ቅኝቶች አሰያየም እና ከቦታው ጋር ያላቸው ተዛምዶ›› በሚል ርዕስ ጥናት ሰርተዋል። በጥናታቸውም ስለአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች ዳሰሳ አድርገዋል።

‹‹ቅኝት ምንድነው?›› ከሚለው እንጀምር። ቅኝት የሚለው ቃል የተገኘው ‹‹ቀነየ›› ከሚለው የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አጀበ ማለት ነው። የሙዚቃ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች ቅኝትን (በእንግሊዘኛው Scale ይባላል) የሙዚቃ ድምጽ ቃና አወቃቀር በሚለው ይስማማሉ። ከነዚህም ውስጥ ለምሳሌ ያህል የተወሰኑትን የሙዚቃ ባለሙያዎች የሰጡትን ትርጉም እንመልከት፣

የሙዚቃ ደራሲ እና ተመራማሪ ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ከዓለማዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች የአቀኛኘት ስርአት እና ከዘፈኖች ድምጽ አወቃቀር አንጻር የሰጡት ትርጉም ።

ቅኝት ድምጾች ባላቸው የድምጽ ቃና ስብስብ (ሬንጅ) እና ርቀት(ከአንደኛው ድምጽ እስከ ሁለተኛው ድምጽ ያለው ርቀት) ይመደባሉ።

በተከታዩ ምሳሌ እንመልከት።

ዲያቶኒክ ------ 8 የድምጽ ቃና ስብስቦች የያዘ

ሄፕታቶኒክ ----7 የድምጽ ቃና ስብስቦች የያዘ

ሄክሳቶኒክ ------ 6 የድምጽቃና ስብስቦች የያዘ

ፔንታቶኒክ ----- 5 የድምጽቃና ስብስቦች የያዘ

ትራ ቶኒክ ------4 የድምጽቃና ስብስቦች የያዘ

ትሪቶኒክ -------3 የድምጽቃና ስብስቦች

የያዙ ናቸው።

እዚህ ላይ አንድ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር አለ፤ ይሄውም የምት እና የዜማ አይነቶችን በጽሑፍ ማስረዳት ከባድ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ሙዚቃ ስንሰማው ቀላል ይመስለናል እንጂ በውስጡ ብዙ ቀመራዊ ስሌቶች አሉት። በብዛት አጥኝዎችም የውጭ ስለሆኑ ቃሉ ራሱ የተለመደ ቃል ላይሆን ይችላል። ለማንኛውም አራቱን የሙዚቃ ቅኝቶች እንያቸው።

**ትዝታ**

ባባህርዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶክተር አስቴር ሙሉ በ2006 ዓ.ም በሰሩት ጥናት ስለ ትዝታ ቅኝት የሚከተለውን ይሉናል።

‹‹የትዝታ ቅኝት በሌላ ስሙ ወሎ ቅኝት ይባላል። ቅኝቱ ስያሜውን ያገኘው ከሚያነሳው ጉዳይ አንጻር ነው። በትዝታ ቅኝት የትናንትን(ያለፈን) ሕይወት የሚያነሱ ግጥሞች ይቀርቡበታል። ያለፈ ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር፣ ትናንት ከዛሬ ጥሩ እንደነበር፣ ትናንት በማለፉ የተሰማን ፀፀት የሚገልጹ ግጥሞች ይቀርቡበታል››

ይህ የትዝታ ቅኝት ሌሎች ዜማዎችን በውስጡ ይይዛል። ለምሳሌ መዲና፣ ዘለሰኛ እና ሙኔ የሚባሉ ዜማዎች የሚገኙት በዚህ ቅኝት ሥር ነው። መዲና እና ዘለሰኛ ለአምላክ ምስጋና የሚቀርብባቸው ዜማዎች ናቸው። ይህ የሆነው ደግሞ ከመሰንቆ አመጣጥ ጋር ተያይዞ ነው። ዛሬ ላይ ሁኔታው ቢቀየርም የመሰንቆ አፈጣጠር አምላክን ለማመስገን ነበር።

በትዝታ ቅኝት ውስጥ የሚገኘው ሌላኛው የዜማ አይነት ሙኔ ነው። ሙኔ በትዝታ ቅኝት ውስጥ ይሁን እንጂ ፈጣንና ለውዝዋዜ የሚጋብዝ ዜማ ነው። በዚህ ዜማ የፍቅር ዘፈን ይቀርባል፣ ገጣሚው ለወደዳት ፍቅሩን ይገልጽበታል። የዜማው ዓይነት ሰቆጣ ተብሎ በሚጠራው የወሎ አካባቢ የሚዘፈኑ ዘፈኖችን ምት የያዘ ነው።

መዲና እና ዘለሰኛ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ግጥሞች የሚቀርቡበት ሲሆን ልዩነቱ በዘለሰኛ ዜማ ውስጥ ‹‹ና ምነው ወዳጄ›› የሚለው አዝማች ይገባል።

**ውስታው ብዙ የእግዚአብሔር**
**አመስጋኝማ ሰው ቢኖር**
**ወልድ በራስህ ኮርተህ**
**ከሰማያት ወርደህ**
**ከድንግል ማርያም ተወልደህ**
**አብ አይበልጥም ወይ አባትህ**
**ተሰማኝ እናትህ**

**በዘለሰኛ ዜማ ውስጥ ደግሞ €€እህ ና ምነው ና ምነው‹‹ የሚለው ይገኝበታል።**

**አምላክ ግብር አርጎ ያበላል ይላሉ**
**አንድ ቀሪ የለም ሁሉም ይጠራሉ**
**አምላኬ ግብርህን እንዳታሳንሰው**
**እምቢ ብሎ አይቀርም አንተ የጠራኸው ሰው**
**እመቤቴ ማርያም ኧረ ተይ ኧረ ተይ**
**ኧረ ተይ ኧረ ተይ ልጅሽን ተቆጪው**
**አንቺ እንደምን አዘንሽ አንድ ቀን ብታጭው**

በአቶ ፋሲል ጥናት ውስጥ ደግሞ ሁለት አይነት የትዝታ ቅኝቶች እንዳሉ እናገኛለን። እነዚህንም ዓብይ(ሜጀር) ትዝታ እና ንዑስ(ማይነር) ትዝታ ይሏቸዋል። የኢትዮጵያ ቅኝቶች የራሳቸው ወጥ ባህርይ ያላቸው ቢሆንም፣ በቀላሉ ለመግባባት ግን ባለ ሰባት ድምጽን እንደ መነሻ በመውሰድ እና በመገንባት በቀላሉ መግባባት ይቻላል። የዚህም ቅኝት የድምጽ ቃና አወቃቀር በ ‹‹C(do) middle C›› እንደ መነሻ በመውሰድ እንመልከት።

ከዓብይ ቅኝት ላይ አራተኛውን ድምጽ እና ሰባተኛውን ድምጽ ሳንጠቀም የምንጫወትበት የቅኝት አይነት ነው።

C ን እንደመነሻ በመውሰድ በ C ዓብይ ዲያቶኒክ ስኬል የምንጠቀምባቸው ድምጾች

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| C | D | E | F | G | A | B | C |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |

ፔንታቶኔክ ስኬል በመላው አለም በተለያየ ቅርጽ በጥንታዊ፣በባህላዊ በሬንታል ሙዚቃ ውስጥ የሚገኝ ነው። ፔንታቶኔክ ስኬል በአብዛኛው መሰረቱ አንድ ሲሆን ነገርግን የተለያየ ቅርጽ አሉት።

**ባቲ**

የባቲ ቅኝት ስያሜውን ያገኘው ወሎ ውስጥ ከሚገኙ አካባቢዎች በአንዱ ነው። ይህ ቅኝት ራሱን ባቲንና ሌሎች የወሎ አካባቢዎችን የሚጠቅስ ነው።

እንደ አቶ ፋሲል ጥናት ባቲ ቅኝት ባቲ የሚለውን ስያሜ ያገኘበት ሁለት ምክንያቶች አሉ። በጣም ታዋቂ ከሆነው ባህላዊ ዘፈን ባቲ የሚል ስያሜ እንዳገኘ እና ይህን ቅኝት በአብዛኛው የሚጠቀሙት ባቲ አካባቢ ወይም ወሎ አካባቢ ያሉ አዝማሪዎች ስለሆነ ነው። ለባቲ ቅኝት እነዚህ ዘፈኖች ምሳሌ ይሆኑናል።

**እረ ባቲ ባቲ ባቲ ገንደ ሲዩ**
**ሀድራው የሚሞቀው ደራርበው ሲተኙ**
**ተይ ድማማ እየ ተይ ድማማ**
**ተይ ድማማ እየተይ ድማማ**
**የማትበሳ ወፍ ተይዛ በጨራ**
**ልቤን አደማችው ቦጭራ ቦጫጭራ**

**አምባሰል**

በወሎ ውስጥ ከሚገኙ ግዛቶች የተሰየመ ነው። በዶክተር አስቴር ጥናት ላይ እንዳገኘነው አምባሰል ‹‹አምባ›› እና ‹‹ሰል›› ከሚሉት ሁለት ቃላት የተመሰረተ ሲሆን አምባ ማለት ተራራ ሰል ማለት ደግሞ ማር ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ የማር ተራራ ብለን ልንጠራው እንችላለን። አካባቢው ማር የሚመረትበት መሆኑ ደግሞ አፋችንን ሞልተን እንድንናገር ያደርገናል። አንዲያውም በአምባሰል ወረዳ ውስጥ ‹‹ማርዬ›› የምትባል ቀበሌ አለች። ቀበሌዋ አብዛኛው ገበሬ ማር የሚያመርትባት ናት።

ወደቅኝታችን እንመለስ። የአምባሰል ቅኝት በቦታው የተሰየመ ስለሆነ በዚህ ቅኝት ውስጥ የሚዘፈኑ ዘፈኖች የአምሳል ተራራንና ታሪካዊ ሁነቶች የሚገልጹ ናቸው። የአምባሰል መልክዓ ምድር ተራራማና ገደል የበዛበት ነው። በታሪካዊነት ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ግማሽ አካል(ግማደ መስቀል) የሚገኝበት የግሽን ደብረ ከርቤ ቤተክርስቲያን የሚገኝበት ነው። ከአምባሰል ቅኝት ዘፈኖች ውስጥ ምሳሌ እንውሰድ።

**አምባሰል ስገደል ምን ያሽማጥጡታል**
**ፈረሰ ባያስጋልብ ሰው ይወጣበታል**
**ግማደ መስቀሉ ተቀምጦበታል**
**ንጉሥና ጳጳስ ይወስድበታል።**
**የአምባሰል ማር ቆራጭ ይወርዳል በገመድ**
**አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ?**

**አንቺ ሆየ**

ለዚህ የሙዚቃ ቅኝት አንድ አፈታሪክ አለ። አንቺ ሆየ በአንድ ወታደር አማካኝነት እንደተፈጠረ ይነገራል። በአንድ ወቅት በተደረገ ዘመቻ ከሚሴ ውስጥ ርቄ በምትባል ቦታ ወታደር ሰፍሮ ነበር። ከሰፈሩት ወታደሮች አንዱ በአካባቢው ካለች አንድ ሴት ፍቅር ይይዘዋል። በልጅቷ ፍቅር ተይዞ ሳለ ጦሩ እንድነሳ ታዘዘ። ይህን ጊዜ ወታደሩ በጣም ተጨንቆ ፍቅሩን ለመግለጽ ‹‹መገን አንቺ ሆየ›› ብሎ አንጎራጎረ። ከዚያ በኋላ ሰዎች ፍቅራቸውን ለመግለጽ ተጠቀሙት። አንቺ ሆየ የሚለውም ቅኝት ሆነ።

‹‹አንቺ ሆየ ቅኝት ከሌሎች ቅኝቶች ለየት ያለ ፀባይ አለው። በጀመረበት የማይጨርስ፣ በጨረሰበት የማይጀምር አወናባጅ ቅኝት ነው›› ይሉታል ዶክተር አስቴር በጥናታቸው። ሌሎች ቅኝቶች በጀመሩበት የሚጨርሱ፣ በጨረሱበት የሚጀምሩ ናቸው። በአንቺ ሆየ ቅኝት እነዚህ ዘፈኖች ይዘፈናሉ።

**አንች ሆየ ለኔ የሚሏት ዘፈን**
**ታጫውተኛለች ብቻየን ስሆን**
**አምና በሬ ገዛች ዘንድሮ ወይፈን።**
**እኔ ጠላ ወዳጅ እሷ ጠላ ወዳጅ**
**የዚህ ጠላ ነገር እኔስ ጠፋኝ ቅጡ**
**እናቲቱ ገብተው እየበጠበጡ።**

ስለአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች ምንነት አይተናል። አንድ ነገር ግን እወቁልን። በእያንዳንዱ ቅኝት ውስጥ ብዙ ሒሳባዊ የሆኑ አሰራሮች አሉ። እንኳን ሒሳባዊ አሰራሮችን የቅኝቶችን ስም እንኳን ለማስታወስ በተቸገርንበት ጊዜ ቀመሮችን ማስቀመጥ የኒኩለር ፊዚክስ ሊሆንብን ነው ማለት ነው። እንዲህ አይነት አገራዊ ፍልስፍና እያለን ነው እንግዲህ የሙዚቃ ትምህርት ቤቶቻችን ሳይቀር በውጭው የተቃኙት። የዘርፉ ሰዎች በዚህ ላይ ሊሰሩበት ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን እስከነ ስማቸውም ቢረሱ አይደንቅም!

# ልዩ ልዩ

## ‹‹ ስልጄ ቫይረሱ በደምሽ ውስጥ አለ ብዬ እንዴት ልንገራት?››

**ወይዘሮ አረጋሽ ዘሪሁን**

**ሰላማዊት ውቤ**

ስሟ አረጋሽ ዘሪሁን ይባላል። ከወላጆቿ ቤት ትዳር ይዛ እንደወጣች ነው ያረገዘቺው። እርግዝናው አስባበትና ፈልጋው ነው የመጣው። የአብራኳ ክፋይ የሆነ የራሷ ልጅ እንዲኖራት ትመኛለች። እናም ትዳር የመሰረተችበት የመጀመርያ ምክንያቷም ልጅ መውለድን ስለምታስብ ነው። ተከታታይ የወሊድ ክትትል ለማድረግ በመጀመሪያ የሄደችበት ቦታ ካዛንቺስ ጤና ጣቢያ ነበር። እናት ልትሆን በመሆኑ ደስተዋ ከመጥን ያለፈ ነበር። ክትትሉን ለመጀመር የሚያስችለው ቅድመ ምርመራ ሲደረግላት ሁሉ ሁለመናዋ ጥርስ በጥርስ ሆኗል። በደሟ ውስጥ የኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረስ እንዳለ ሲነገራት ግን ዙርያ ገባው ጨለማ ሆነባት። መሬት ተከፍታ እንድትውጣት ሁሉ ተመኝታ እንደነበር ታስታውሳለች።

‹‹በፍፁም እውነታውን ልቀበል አልቻልኩም። ምክንያቱም ባለቤቴ ሹፌር ቢሆንም መስክ የሚያስወጣ ሥራ የለውም። በቤተሰቡ ላይ ማግጦ እንዲህ ዓይነት ችግር ያመጣልም ተብሎ አይታማም። ሆኖም ለብዙ ጊዜ እንዴት መጣና ማን አመጣው እየተባባልን ተፋጥጠን ቆይተናል። አንዳችን አንዳችንን ብንጠረጥርና ሺህ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ብንወያይም ቫይረሱ በማናችን ሳቢያ እንደመጣ ማወቅ አልቻልንም።›› የምትለው ባለታሪካችን፤ ቆይቶ የሰፈር ልጆች ተሰባስበው የሚያግዙት አንድ ወጣት እንደነበረ ትዝ እንዳላት ትናገራለች።

ይህ ወጣት ነፍሱን ይማረውና ለእናቱ አንድ ነው። በተኛበት አልጋ ላይ የሚያደርጉለት እንክብካቤና ድጋፍ ይሄን ሰብኣዊነት ታሳቢ ያደረገ ነበር። ሆኖም በፍፁም የደም ንክኪ እንዳልነበራቸው እርግጠኛ በመሆኗ ወጣቱን መጠራጠሯን አቆመች። ዜናው ሲነገራቸው መሬት ላይ ተንበርክካ ፀጉሯን እየነጨች የጀመረቺውን ለቅሶ ለዓመታት አላቋረጠቺውም። የአርባ ቀን ዕድሏን በፀጋ መቀበል አቅቷትም ሌት ተቀን ትንሰቀሰቅ ነበር። አሸዋ ላይ ተንበርክካ ስታነባ ኖራለችም። በእጅጉም በሕይወት በመኖሯ ተስፋ ቆርጣለች።የካዛንቺስ

> ‹‹ ያኔ ዘመኑ ጨለማ ነበር። ያኔ የመድሃኒት እጥረት ነበር። አሁን ግን ጊዜው የብርሃን ዘመን ነው፡፡ ማንኛውም ቫይረሱ በደሙ ያለበት ሰው መድሃኒት የሚጀምርበት ጊዜ ላይ ተደርሷል ››

ጤና ጣቢያ የምክር አገልግሎት ባለሙያዎች በቀላሉ ሊያረጋጓት እንኳን አልቻሉም ነበር። በዚህ የተነሳ በሪፈር ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እስከመላከም ደርሳለች።

‹‹ሆስፒታሉ በፊናው ንጋት በተሰኘና አሁን የት እንዳለ የማላውቀው ፕሮጀክት ውስጥ እንድታቀፍ አደረገኝ። ይሄኔ ሲዲ ፎሬ 900 በመሆኑ መድሃኒት አላስጀመሩኝም። ፈጥኖ መድሃት የሚጀምረው ሲዲ ፎሩ 500 የሆነ ነው። የባለቤቴ የሲዲ ፎር መጠን እዚህ መካከል በመሆኑ መድሃኒት የጀመረው ቀድሞኝ ነው። ቆየት ብዬም እኔ ሲዲ ፎሬ 900 ቢሆንም በማርገዜ ምክንያት መድሃኒት ተጀመረልኝ።›› የምትለው አረጋሽ፤ በንጋት ፕሮጀክት አማካኝነት እርሷን ጨምሮ 50 ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው እናቶችን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሰባተኛ ፎቅ ላይ ልጆቻቸውን እንዲወልዱ እንደተደረጉ ታስታውሳለች።

‹‹በየጊዜው አንድ ፌስታል ሙሉ ኪኒን ተሸክሞ መግባት ይሰለቻል። በየቀኑ እስከ 10 ፍሬ የሚደርሰውን መድሃኒት መቃሙም መፈጠርን ያስጠላል። ልጄ በፈሳሽ መልክ የምትወስደው መድሃኒት በራሱ ራሱን የቻለ ራስ ምታት ሆኖብኝ ቆይቷል። ልጄ መድሃኒቱን ከወሰደች በኋላ ከ30 ደቂቃ በፊት ካስመለሳት የግድ ተደግሞ ይሰጣታል። በየጊዜው ለፈጣሪዬ እያለቀስኩ ነበር። መድሃኒቱ ዳግመኛ የመስጠቱ ጉዳይ በእጅጉ ያማርረኝ ነበር። በየጊዜው በምሬት ወደ ፈጣሪዬ አልቅሻለሁ።›› ትላለች ትናንትን በትዝታ ስታስታውሰው።

ትቀጥልናም ‹‹ያኔ ዘመኑ ጨለማ ነበር። ያኔ የመድሃኒት እጥረት ነበር። በመሆኑም ለረጅም ጊዜ በሲዲፎር መጠን ነበር ተገድበን የቆየነው። ከሦስት መቶ እያለ ነው 500 የገባው። ያኔ እኔ ከ800 እስከ 1ሺህ ይደርስ ነበር ሲዲ ፎሬ። በማርገዜ ነው እኔ ሲዲ ፎሬ 900 እያለ መድሃኒት ልጀምር የቻልኩት ።አሁን ላይ ማንኛውም ቫይረሱ በደሙ ያለበት ሰው መድሃኒት የሚጀምርበት ጊዜ ላይ ተደርሷል። የደረስንበትን ጊዜ የብርሃን ዘመን ካሰኘኝም እንዱ ይሄ ሁኔታ ነው።›› ትላለች።

ሐኪም ያላትን በመተግበሯ ውጤታማ እንደሆነች፤ ለዚህ ያበቃትም በአግባቡና በሰዓቱ መድሃኒት መውሰዷ መሆኑን ትናገራለች። ቤት ያፈራውን መብላት መጠጣት ሌላው ነው። በእርግዝና ሰዓት ዋናውን የፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት መውሰዷ፣ ልጇ ከተወለደች በኋላ ጡት እያጠባች የምትወስደውን መድሃኒት እስከ ስድስት ወር ድረስ በአግባቡ መከታተሏ ብዙ ነገሯን እንደቀየረውም ታስረዳለች።

ለልጇ በርካታ እንክብካቤዎችን አድርጋለች። እስከስድስት ወር በጡት ከስድስት ወር በኋላምደግሞ በምግብ እየተንከባከበቻት ቆይታለች። ከዚያ ጎን ለጎን በፈሳሽ መልክ መድኃኒቱን እንድትወስድም አድርጋታለች። መድሀኒቱ ከዘጠነኛ ወር በኋላ የተቋረጠ ሲሆን፤ የመጀመርያ ምርመራ እንድታደርግ አደረገቻት። በዚህም በወቅቱ የሰማችው ነገርም የሚያስደስት ሆነላት። ልጇ በተደረገው ምርመራ ነፃ ነሽ ተባለችላት። ከዓመት ከስድስት ወር ቆይታ በኋላ ደግሞ ነጻ ማረጋገጫ ምርመራ እንድታደርግ ወደ ሀኪም ቤት ወስዳት አሁንም ነፃ እንደሆነች ተነገራት። የዚህን ጊዜ እልል ነበር ያለቺው። ይህ ደስታ ግን እስከመጨረሻው የዘለቀ አልሆነላትም። ሁለተኛ ልጇን ባላሰበቺው ሁኔታ አርግዛ ነበርና በቀደመቺው ልጇ ልክ ልትታደጋት አልቻለቺም።

‹‹ ሁለተኛ ልጄን ማርገዜን ያወቅኩት ለሌላ ምርመራ በሄድኩበት አጋጣሚ ነው። መዘናጋቴ ራሴን ቢያስወቅሰኝም የመጀመርያዋን ባዳንኩበት አግባብ ላድናት ሞክሬ ነበር። ሙከራውን ለመተግበር ብዙ ጥረት ሳደርግም ቆይቻለሁ። በእርግጥ ቀድሜ በአልትራ ሳወንድ ስላልታየሁ የምወልደው ወንድ ይሁን ሴት አላወቅኩም። ቢሆንም ዘር ለማብዛት እግዚአብሄር የሠጠኝን ለመቀበል ተስፋ አድርጌ ሳይሆን ድንገት ሳይታሰብ ያረገዝኳት አሁንም ሴት ነበረች። ሂደቱ አድካሚ በመሆኑ ምንም ያህል ልጠነቀቅ ብሞክርም የቱ ጋር ስህተት እንደፈፀምኩ አላውቅም። ዘጠኝ ወር ደርሶ ሴት ልጅ ወለድኩ። ስትመረመር ቫይረሱ በደሟ ተገኘባት። የጤና ባለሙያዎች ከዚህ በኋላም ልጄን ከቫይረሱ ነፃ የሚያደርጋት መፍትሄ እንዳለ በሚያውቁት ልክ ምክራቸውን ለግሰውኛል። ሆኖም ሜሪ ነፃ ልትሆንልኝ አልቻለችም።›› የምትለው አረጋሽ፤ በምግብና በተለያየ መንገድ ብሎም እሷ በማታውቀው መድሃኒት ስለምትንከባከባት እንኳን ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ያለ ምንም ጉዳት የደረሰባት አትመስልም። ቆንጆና ድንቡሽቡሽ ያለች ነች።

‹‹ ከመጀመርያው ጀምሮ እስከ እዚህ ድረስ መዘናጋቴ እራሴን የልጄ ገዳይ አድርጌ እንድቆጥር አደረገኝ። ደግሞም ቫይረሱ በደምሽ ውስጥ አለ ብሎ የመንገር ድፍረት አሳጣኝ። እንዴት ልንገራት?›› እያለች ራሷን በሰቀቀን ውስጥ የከተተቺው አረጋሽ፤ ለእንደእርሷ አይነት ሰዎች ምክር አላት። ይህም በማንኛውም ጊዜ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይም የኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ የየቀኑ ሥራችን መሆን አለበት። ምክንያቱም ራሳችን ባንድንም ለምንወልዳቸው ልጆች እንድንደርስላቸው እንሆናለን ትላለች። እውነት ነው መመርመር ከብዙ ነገር ይጠብቃልና ምክሯ ተግባራዊ ይሁን በማለት ሀሳባችንን ቋጨን።

# ዓለም አቀፍ

## ፌንታሊን የተባለ አደገኛ ገዳይ ዕጽ መያዟን አሜሪካን አስታወቀች

እየተጠናቀቀ ባለው እኤአ በ 2022 መላውን የአሜሪካ ዜጋ ለመግደል በቂ የሆነ ፌንታሊን የተሰኘ አደገኛ አደንዛዥ ዕጽ መያዙን የአሜሪካ የዕጽ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አስታወቀ። የዕጽ ቁጥጥር አስተዳደር (ዲኢኤ) በአንዴ እንዲወሰዱ ተደርገው የተዘጋጁ እያንዳንዳቸው ሁለት ሚሊ ግራም የሚመዝኑ ገዳይ የሆኑ 379 ሚሊዮን ፌንታሊን የተሰኘ ዕጾችን ይዣለሁ ብሏል።

ባለሥልጣኑ እንደሚለው ይህ አደንዛዥ ዕጽ ከሄሮይን 50 እጥፍ በላይ ገዳይ መሆኑን አመልክቶ፣ ፌንታኒል አሜሪካ በአሁኑ ወቅት የገጠማት ገዳይ ስጋት ነው ሲል ገልጾታል። ኤጀንሲው እንደሚለው ከሆነ ከፍተኛ መጠን ያለው ፌንታሊን ወደ አሜሪካ የሚገባው ከሜክሲኮ ነው። ዲኢኤ ከ4 ሺህ 500 ኪሎ ግራም በላይ ፌንታሊን እና 50.6 ሚሊዮን በእንክብል መልክ የተዘጋጁ ዕጾችን ይዟል።



ለዕጹ መጠቀሚያነት የዋሉ መርፌዎች

ኤጀንሲው እንዳለው በእንክብል መልክ የተዘጋጁት ዕጾች ህመም ማስታገሻ መድኃኒቶች እንዲመስሉ መደረጋቸውንም ጨምሮ ገልጿል። እየተጠናቀቀ ባለው በዚህ የፈረንጆቹ ዓመት የተያዘው የዕጽ መጠን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ ጨምሯል።

በአሜሪካ የሚያዙት ዕጾች በሲናሎዋ እና ጃሊስኮ ዕጽ አዘዋዋሪ ቡድኖች አማካይነት ሜክሲኮ ውስጥ በምስጢራዊ ስፍራ በሚገኙ ፋብሪካዎች በገፍ ይመረታሉ። ኤጅንሲው እንዳለው ከሆነ ደግሞ ዕጹን ለማምረት ግብዓቱ የሚመጣው ከቻይና ነው።ፌንታሊን እጅግ አደገኛ የሆነ ዕጽ ሲሆን የእርሳስ ጫፍ ላይ ልትቀመጥ የምትችል ትንሽ መጠን ሰውን የመግደል አቅም አላት።

ባለፈው ዓመት 100 ሺህ አሜሪካውያን ከመጠን በላይ ዕጽ ወስደው ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን፣ ከዚህ አሃዝ ውስጥ ሁለት ሦስተኛው ሞት ከፌንታሊን ጋር የተገናኘ ነው።በዚህ ዓመት የተያዘው ፌንታሊን መጠን 330 ሚሊዮን የአሜሪካ ነዋሪዎች መግደል የሚችል ስለመሆኑ ኤጀንሲው አመልክቷል፡፡

“የዲኢኤ ቀዳሚው ዓላማ በሜክሲኮ ያሉትን ግዙፍ ዕጽ አዘዋዋሪ ቡድኖች - ሲናሎዋ እና ጃሊስኮ ማሸነፍ ነው። ዛሬ ላይ አሜሪካውያን በፌንታሊን እንዲሞቱ ምክንያት እየሆኑ ያሉት እነዚህ ሁለት ቡድኖች ናቸው” ሲሉ የኤጀንሲው አስተዳዳሪ አን ሚልግራም ተናግረዋል።

ከፌንታሊን በተጨማሪ ዲኢኤ 60 ሺህ ኪሎ ግራም ሜታአምፌታሚን እና ወደ 2 ሺህ ኪሎ ግራም ሄሮይን እንዲሁም 200 ሺህ ኪሎ ግራም ኮኬይን መያዙን ማስተወቁን ቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል፡፡

## ታሊባን የአፍጋኒስታን ሴቶች ዩኒቨርሲቲ እንዳይገቡ አገደ

አፍጋኒስታንን ከሁለት አስርት በኋላ ዳግም እያስተዳደረ የሚገኘው ታሊባን ሴቶች ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዳይገቡ አግዷል። የሀገሪቱ የትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው ደብዳቤ እንደሚያሳየው የተለየ ትዕዛዝ እስኪመጣ ድረስ የመንግስትም ሆነ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሴቶችን ተቀብሎ ማስተማር አይችሉም።የታሊባን አስተዳደር ካቢኔ ይህን ውሳኔ ያሳለፈው የመንግስታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በአፍጋኒስታን ጉዳይ ለመምከር ቀጠሮ በያዘበት እለት ነው።

ተመድ፣ አሜሪካ፣ ብሪታንያ ዳግም ስልጣን የተቆናጠጠው ታሊባን የሴቶችን መብት ያሻሽላል ተብሎ ሲጠበቅ ከዩኒቨርሲቲ ትምህርት እስከማገድ የደረሰ ውሳኔ ማሳለፉን ተቃውመውታል። ውሳኔን የመንግስታቱ ድርጅትን ጨምሮ በርካታ ሀገራትና ተቋማት እየተቃወሙት ነው፡፡ ታሊባን በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ይሁንታን ያገኘ ዘንድ የአፍጋኒስታናውያንን ሰብአዊ መብትና በተለይ የሴቶችን ነጻነት ሊያከብር ይገባል ብለዋል በመንግስታቱ ድርጅት የአሜሪካ ረዳት አምባሳደር ሮበርት ዉድ።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ቃል አቀባይ ኔድ ፕራይስም ዋሽንግተን ታሊባንን ተጠያቂ ለማድረግ እያጤነች ነው ማለታቸውን ሬውተርስ አስነብቧል። በተመድ የብሪታንያ አምባሳደር ባርባራ ውድዋርድ በበኩላቸው፥ የታሊባን ውሳኔ በየትኛውም አካባቢ የምትገኝን ሴት የሚያስከፋ የሰብአዊ መብት ገፈፋ ነው ሲሉ ገልጸውታል።

በመጋቢት ወር 2022 ሴቶች ብቻ የሚማሩበት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እከፍታለሁ የሚል ቃል የገባው ታሊባን፥ አሁን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሴቶችን እንዳያስተናግዱ አሳስቧል። የመንግስታቱ ድርጅት ቃል አቀባይ ስቴፋኒ ዱጃሪክ በኒዮርክ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ታሊባን የሚገባውን ቃል ማፍረሱን ገፍቶባታል፤ ሀገሪቱን ያለ ሴቶች ተሳትፎ እንዴት ሊመራት እንዳቀደም ማሰብ ይከብዳል ብለዋል።

በመንግስታቱ ድርጅት የአፍጋኒስታን ልዩ መልዕክተኛ ሮዛ ኦቱንባየቫ የካቡልን ውሳኔ እንደሰሙ በጸጥታው ምክር ቤት ባሰሙት የተቃውሞ ድምጽ፥ አለም አቀፉ ማህበረሰብ ታሊባንን መታገስ አብዝቷል ነው ያሉት።ታሊባን የሴቶችን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ እንዲታገድ ያዘዘው ተማሪዎች ለፈተና ዝግጅት ላይ እያሉ ነው።በርካታ ተማሪዎችም



ይህን ውሳኔ በመስማታቸው በከፍተኛ መረበሽ ውስጥ መሆናቸውን ነው ሬውተርስ ያነጋገራቸው አፍጋናውያን የተናገሩት።

ታሊባን በመስከረም ወር 2021 የአሜሪካ መራሹ ጦር አፍጋኒስታንን ለቆ መውጣቱን ተከትሎ ከሁለት አስርት አመታት በኋላ ስልጣን ዳግም ይዟል።መንግስት ሆኖ ሀገር እየመራ ያለው ታሊባን በሴቶች መብት ላይ ማሻሻያ እንደሚያደርግ ቢገልጽም ሴቶች በፓርኮች እና የስፖርት ማዘውተሪያዎች እንዳይገኙ የሚያስገድድ መመሪያ ሲያወጣ ጊዜ አልወሰደበትም ሲል አል ዐይን ዘግቧል።




አዲስ ዘመን ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# እየሳሳ የመጣው የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የአገር አቋራጭ ውድድሮች ውጤት

**ብርሃን ፈይሳ**

ይህ ወቅት በአትሌቲክስ ስፖርት በብዛት የአገር አቋራጭ ውድድሮች የሚካሄዱበት ነው። በመሆኑም የተለያየ ደረጃ የተሰጣቸው የአገር አቋራጭ የዙር ውድድሮች በተለያዩ ከተሞች እየተካሄዱ ይገኛሉ። በፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ሁለተኛ ወር አጋማሽ ደግሞ በዓለም አትሌቲክስ አዘጋጅነት የሚከናወነው የዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ይካሄዳል። ይህንን ውድድር ዘንድሮ ለ44ኛ ጊዜ የምታስተናግደው አውስትራሊያ ናት።

ይህ ውድድር እአአ ከ1973 ጀምሮም ሳይቋረረጥ እአአ እስከ 2019 ድረስ ቢካሄድም በኮቪድ 19 ወረርሽን እና ሌሎች ምክንያቶች እየተራዘመ በ2023 ይካሄዳል። በዚህ ውድድር ላይ የምስራቅ አፍሪካ አገራት በውጤት ረገድ የበላይነቱን የያዙ ሲሆን፤ በተለይ ኬንያ እና ኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት አላቸው። ይሁንና በወንዶች በኩል እአአ ከ2013 ጀምሮ ኢትዮጵያ የምትታወቅበትን ውጤታማነት ይዛ መቀጠል አልቻለችም። በ2019 ደግሞ በግል የሜዳሊያ ሰንጠረዥ ውስጥ መግባት አልቻለችም፤ በቡድንም ሶስተኛ ነበረች።

ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በረጅም ርቀት ውድድሮች ስኬታማ መሆናቸው ይታወቃል። ልምምድ የሚያደርጉባቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎችና የመልከዓ ምድር አቀማመጥም በርካታ መሰናክሎች ባሉት አገር አቋራጭ ውድድር ስኬታማ ለመሆን ምክንያት



**በአለም አገር አቋራጭ ውድድሮች ኢትዮጵያውያን የሚያስመዘግቡት ውጤት እየቀነሰ መጥቷል፣**

ሆኗቸዋል። በኢትዮጵያም በአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ የሚዘጋጀውና በዓለም አትሌቲክስም ዕውቅና የተሰጠው ብቸኛው ዓለም አቀፍ ውድድር የጃንሜዳ አገር አቋራጭ ውድድር ነው። በመሆኑም አገር አቋራጭ ውድድሮች ለኢትዮጵያ እንደሌሎች ረጅም ርቀት ሩጫዎች ሁሉ ውጤት ሊመዘገብበት የሚችል የሩጫ ዘርፍ ነው ለማለት ይቻላል።

በእርግጥም እንደ መሃመድ ከድር እና ቀነኒሳ በቀለ ያሉ አትሌቶች በዚህ ርቀት ያገኟቸው አስደናቂ ድሎች ለዚህ ማስረጃ ይሆናሉ። የዓለም አቀፉ ሻምፒዮና የኢትዮጵያ ተሳትፎ መነሻውን የሚያደርገው እአአ በ1981 ነው። በስፔን ማድሪድ በተካሄደው በዚህ ውድድር ላይም መሃመድ ከድር የመጀመሪያውን የብር ሜዳሊያ በማጥለቅ ታሪካዊ አትሌት ሊሆን ችሏል። አትሌቱ በቀጣዩ ዓመት ውድድሩን በቀዳሚነት ሲያጠናቅቅ፤ እአአ በ1983 ደግሞ በቀለ ደበሌ ድሉን ማስቀጠል ችሏል። ወዳጆ ቡልቲ እና አበበ መኮንን እአአ በ1985 እና 1986 የነሃስና የብር ሜዳሊያ ቢያስመዘግቡም፤ እአአ እስከ 1991 ባለው ጊዜ ደግሞ ውጤታማነቱ ተቋርጦ ነበር። እአአ በ1992 ፊጣ ባይሳ ኢትዮጵያን ወደ ሜዳሊያ ባለቤትነት ሲመልሳት፤ ኃይሌ ገብረስላሴ እና አሰፋ መዝገቡም በዚህ ሻምፒዮና በተለያዩ ጊዜያት ለአገራቸው ሜዳሊያ ማስገኘት ችለዋል።

በዚህ ውድድር ኢትዮጵያ ወደ አስደማሚ የስኬት ዘመን የተሸጋገረችው እአአ 2002 ላይ ነው። የአየርላንዷ ደብሊን አዘጋጅ በነበረችበት በዚህ ውድድር ላይ የአገር አቋራጭ ውድድሮች ንጉሱ ቀነኒሳ ለመጀመሪያ ጊዜ መድረኩን በድል ሊቀላቀል ቻለ። ከዚያ በኋላ ባሉት አምስት ተከታታይ ዓመታትም አትሌቱ የውድድሩን የበላይነት ጠቅሎ መያዝ ችሏል። ከአንድ አመት መቋረጥ በኋላም እአአ 2008 ላይ በድጋሚ ወደ ድሉ ሲመለስ በአጠቃላይ 6 የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ በመድረኩ ቁጥር አንድ አትሌት ነው። አትሌት ገብረእግዚአብሄር ገብረማርያም፣ ስለሺ ስህን፣ ኢማና መርጋ፣ ሙክታር እድሪስ እና አባዲ ሃዲስም በመድረኩ ውጤታማ መሆን የቻሉ አትሌቶች ናቸው።

በአጠቃላይም ኢትዮጵያ በወንዶች የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና 10 የወርቅ፣ 6 የብር እና 8 የነሃስ በድምሩ 24ሜዳሊያዎችን ማግኘት ችላለች። በቡድን ደግሞ 10 የወርቅ፣ 13 የብር እና 8 የነሃስ ሜዳሊያዎች ተመዝግበዋል። ይህ ውጤትም ከኬንያ ቀጥሎ የሚቀመጥ ውጤት ነው፤ ይሁንና ውድድሩ በየሁለት ዓመቱ መካሄድ የጀመረበት እአአ ከ2011 አንስቶ ይህ ውጤታማነት እየሳሳ መምጣቱን ባለፉት አመታት የተመዘገቡ ውጤቶች ማሳያ ናቸው። ለዚህም እንደምክንያት ከሚነሱት ነጥቦች መካከል በሻምፒዮናው ተሳታፊ የሚሆኑት አትሌቶች በአገር ውስጥ በሚካሄዱ ውድድሮች የሚመረጡ መሆኑ የውጤት መቀዛቀዝ ፈጥሯል።

በተለይ ክለቦች እና ክልሎች ታዋቂ አትሌቶችን በአገር ውስጥ ውድድሮች እንዲሳተፉ በማድረግ ረገድ ሚናቸውን በትክክል እየተወጡ አለመሆኑንም ለውጤቱ መቀዛቀዝ ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ምክንያት መሆኑን ባለሙያዎችም የሚስማሙበት ነው። አትሌቶች በማራቶን ውድድሮች ላይ ትኩረት ከማድረጋቸው ጋር ተያይዞም የአገር አቋራጭ ውድድሮች የቡድን ውጤት ላይ ተፅእኖ ማሳደሩ ይታመናል።


## ማረሚያ

ታህሳስ 9 ቀን 2015 ዓ.ም በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገጽ 37 በአቶ ሲራጅ መሐመድ ስም በወጣው የሊብሬ መጥፋት ማስታወቂያ የሰሌዳ ቁጥር 1-88900 አሮ ተብሎ የወጣው በስህተት ስለሆነ የሰሌዳ ቁጥር 1-85900 አሮ ተብሎ ተስተካክሎ ይነበብ፡፡

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ክልል በአ.አ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 8ቀበሌ የቤት ቁጥር ሺድ በ 0059037317 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለሚታወቀው ኦሉማ ቦቴ እና ጓደኞቻቸው የቢሮ ፈርኒቸሮችን ማምረት ህብረት ሽርክና ማህበር በግብር /ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ከ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ከምጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር ጥቅም ላይ የዋለ እና ጥቅም ላይ ያልዋለ ከ001 እስከ 250 አስር ፖድ /5/ ደረሰኝ የ የእጅ በእጅ ደረሰኝ (ቲኦቲ) ስለጠፋብን በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸሙ በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር /ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር /ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲደረግ እጠይቃለሁ፡፡

**ኦሉማ ቦቴ እና ጓደኞቻቸው የቢሮ ፈርኒቸሮችን ማምረት ህብረት ሽርክና ማህበር**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ብረሃኑ እንደሻው ጌቼ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-87881 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር WJME3TRS40C359070 ሞዴል AT380T38H የሞተር ቁጥር F3BEE681G*B220-250043* የሊብሬ ቁጥር 0058801/0072998 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አንጎላ ኤምባሲ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-82-009 የሻሲ ቁጥር MR1YX59G6A3013747 የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻሲ ቁጥር MR1YX59G6A3013747 ሞዴል TGN51L የሞተር ቁጥር 2TR6834492 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 12/4/2015 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ሀኪት ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

ለ ሐኪት ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዮኖች በሙሉ፤

የሐኪት ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዮኖች ዓመታዊ ጠቅላላ መደበኛ ስብሰባ ጥር 9 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ በራስ ሆቴል መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ስለሚካሄድ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቦታ ቀንና ሰዓት እንድትገኙ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የስብሰባ ጥሪ ያቀርባል፡፡ በአዲሱ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 370 እና 371 ድንጋጌዎች መሠረት፤

i. የማህበሩ ስም ሐኪት ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር

ii. የማህበሩ ዓይነት፤ አክሲዮን ማህበር

iii. የማህበሩ ዋና ገንዘብ፤ ጠቅላላ የተከፈለ ብር 81,650,000.00 /ሰማንያ አንድ ሚሊየን ስደስት መቶ ሀምሳ ሺ ብር/

iv. ዋና መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ፤ አ/አበባ ከተማ፤ ቂርቆስ ክ/ከተማ፤ ወረዳ 08፤ የቤት ቁጥር 388/610 ባህራን ሞል 6ኛ ፎቅ፤ ቢሮ ቁጥር 610

1. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ መደበኛ ጉባዔ አጀንዳዎች፤

- ዕለቱን የስብሰባ አጀንዳዎች ማፅደቅ፤

1.1. የማህበሩን የዳይሬክተሮች ቦርድ የ2014 ዓ.ም የበጀት ዓመት የስራ ክንውን ሪፖርት ማድመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፤

1.2 የማህበሩን የውጭ ኦዲተር ምርጫን ማጽደቅ፤

1.3. የተጓደለ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ምትክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ምርጫ ማከናወን፤እና

1.4. በማህበሩ በኩል እንዲገዙ የተደለደሉላቸውን አክሲዮኖች ዋጋ ሙሉ በሙሉ አጠናቀው ለማህበሩ ገቢ ባላደረጉ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ላይ ተወያይቶ መወሰን ናቸው፡፡

**ማሳሰቢያ፤**

የማህበሩ ባለአክሲዮኖችም ሆኑ እነዚህኑ ባለአክሲዮኖች በመወከል በጠቅላላ ጉባዔ ላይ በውክልና የምትሳተፉ ወኪሎች ህጋዊ የውክልና ስልጣን ማረጋገጫ ሰነድ እና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም አቻ መታወቂያ እና የእነዚህኑ ሰነዶች የተገናዘቡ ኮፒ ይዛችሁ በስብሰባው ላይ እንድትገኙ እናስታውቃለን፡፡

**የሐኪት ኮንስትራክሽን አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ**


በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ